# ታጠቅ

በኤውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሔት

ሚያዝያ 1968 ዋጋው የኢ.ት $ 1.75

## በኤውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ

| | |
|---|---|
| ኃይሌ ፊዳ | ፕሬዚደንት |
| ታደሰ ገሠሠ | ዋና ጸሐፊ |
| ጴጥሮስ ወ ገብርኤል | ም ጸሐፊ |
| ብርሃኑ ወልደየስ | ገንዘብ ያዥ |
| እንጉዳይ በቀለ | አባል |

## የታጠቀ አዘጋጅ ቦርድ

| | |
|---|---|
| ገርማ በሻህ | አዘጋጅ |
| ኃይሌ ፊዳ | የዝግጅት መዘር |

# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| ርእስ አንቀጽ | | |
| የኢት የሃሳብ ነጻነትና የጋዜጣ ሁኔታ | ገጽ | 1 |
| የኤርትራ ሕዝብ ትግል | | 14 |
| ቤቱ እንዳይፈርስ አድሃሪ እንዳይነግሥ | | 25 |
| ኢምፔሪያሊዝምና የ3ኛ ዓለም ፕሮግራሽን | | 29 |
| የመጽሐፍ ትችት | | 43 |
| ከደብዳቤ ሳጥናችን | | 54 |
| ልዩልዩ ጉዳዮች | | 55 |
| ካዲስ አበባ ሁለት ዜናዎች | | 57 |


# ርእስ አንቀጽ

## የነጻነት ትግል

በዚህ ወር መጀመርያ የኢትዮጵያ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ባዲስ አበባ የፈጸሙትን ትግል በመደገፍ በኤውሮፓ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሁሉ ከዚህ ትግል ጋር ያላቸውን አንድነት ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ያሁኑ ጊዜ ሕብረሰብአዊ ዋና ብሮብሌም ለሕዝቡ የዲሞክራሲ ትግልና የኑሮ መሻሻል ትግል ትልቅ እንቅፋት የሆነው ያሁኑ ባላባታዊ ገዥ ነገሥት መንግሥት ነው። ይህ መንግሥት ሕዝቡን ለማገልገል የማይችል እንዲያውም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድህነትና ወደኋላ መቅረት ዋና ምክንያት መሆኑ ግልጽ ሆኗል። እስካሁን ድረስ እድሜውን አራዝሞ ለመኖር መቻሉ ሕዝቡን እየከፋፈለ በማጋጨት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት፣ በዓለም ፊት በመግደርደር፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋሻ መከታ በማድረግ ነው። ነገር ግን ለጊዜው በመፋፋም ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነት ትግል የተደበቀውን ያገሪቱን እውነተኛ ሁኔታ ለዓለም በግልጽ አሳይቷል። በመሸፋፈንና በመቀባት እስካሁን ድረስ እፍኝ ያቀየው እውነት በይፋ ስለታወቀበት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በንዴት በሰላማዊው ሕዝብ በማሰርና በመፍጀት ያረመኔ ተግባሩን በመፈጸም ላይ ይገኛል። ዳሩ ግን ምንም እንኳ የመንግሥቱ ያረመኔ ተግባር በየጊዜው እየጠነከረ ቢሄድም ከባላባት አገዛዝ ነጻ ለመውጣት እስከመጨረሻው ድል ድረስ ለመታገል ቆርጦ የተነሣውን የኢትዮጵያን ሕዝብ መንፈስ ከቶ ሊሰብረው አልቻለም። ሕዝቡ አሁን ካለበት የባርነት መደብ አርነት እስኪወጣ ድረስ በኢትዮጵያ ከቶ ሰላም ሊኖር አይችልም። ባዲስ አበባ የተደረገው የተማሪዎች ወገኖቻችን ትግል በሁኑ ጊዜ ሠራተኞችና ገበሬዎች ከሚያደርጉት ትግል የተለየ አይደለም። የተማሪዎች ትግል የሕዝብ ትግል ነው።

ሠራተኛው ገበሬውና ተማሪው በጠቅላላውም የተጨቆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያደርገው ትግል ካሁኑ ጉልህና የተጨበጠ ውጤት አስከትሏል::በቦረና በባሌ በኤርትራ የሚገኘው ገበሬውና ሠራተኛው ሕዝብ ከባላባት አገዛዝ ጭቆና ነጻ ለመውጣት የሚያደርገው ትግል የከረረ ፀርነት ሆኗል::የመንግሥቱ ያረመኔ ተግባር መፈጸሚያ መሣርያ የሆኑት የጦር ሠራዊትና የፖሊስ ኃይል እንደ ፉከራቸውና እንደተመኩባቸው ባይሆኑ በርግጥ መሣርያ ብቻ ሊፈቱ የሚችሉ የወረቀት አንበሶች መሆናቸውን አሳይቷል::ይልቁንም የመንግሥቱ ዋና መመኪያ ጋሻ የነበረው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቬትናም ላይ ታስሮ በመደብደብ ላይ ስለሚገኝ እንዲሁም በኢኮኖሚው መድከም ምክንያት በገንዘብ ችግር ላይ ስለወደቀ እንደቀድሞው በገፍ ወታደራዊ እርዳታ ሊሰጥ በለመቻሉ በሳባታዊው የንጉሠ ነገሥት መንግሥቱ በትልቅ ሽብር ላይ ይገኛል::ከመንግሥቱ ጋር ተሻርከው የኖሩ አበሳብዮች እንኳ መንግሥቱ ከአገሪቱ ወዲህ የደህንነታቸው ዋስትና ሊሆናቸው የማይችል: እራሱም በስጋት ላይ የሚገኝ መሆኑን ስለተረዱት በገዛቸው ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ይሞክራሉ::ይህ ሁሉ የሚያበየው አድሃሪውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ለመጣል የተነሡትን ሕዝባዊ ኃይሎች ግን ሊገታቸው እንደማይችልና እንደዚሁም በሳባታዊው አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝም ከገሬችን ገጽ የሚጠፉበት ቀን የተቃረበ መሆኑን ነው::

ባጭሩ ያሁኑ ባሳባታዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ደጋፊዎች እምነት ያልጣሉበት: በሠራተኛውና በገበሬው ሕዝብ ዘንድ የተጠላ: በዓለም ፊት የተናቀና የተሳቀበት መቃብሩን በመቆፈር ላይ የሚገኝ ነው::ነገር ግን ከዚህ ላይ በተለይ ሊታወስ የሚገባው አንድ መደበኛ የሕብረሰብ ሕግ አለ:: ይኸውም ተንኩሉ የተገለጸበት ምኞቱ ያልተሳካለት የሕዝብ ትግል አመንምኖት ወደመውደቅ የቀረበ አድሃሪ አገዛዝ አስከመጨረሻ ድረስ በመታገል ጭቆናውንና ያረመኔ ተግባሩን አያበበስ አስከአለተቀቱ ድረስ በመፍጨርጨር የማይቀጠብ



መሆኑ ነው::ኢምፔሪያሊዝምና አድሃሪዎች ተጠርገው ከልጣፉ በስተቀር ድል መንሣታቸውን አያምኑም: አሚን ብለው አይቀበሉትም::ከነርሱ መውደቅ በኋላ ሌላ ትውልድ እንዳይከተል ሌላ ሕብረሰብም እንዳይታነጽ ለመከልከል ማናቸውንም የኑሮ መሠረቶች አበላሽቶ ከመሄድ አይመለሱም::በዚህ ወር በሳባታዊው የንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፈጸመው የፋሺስት ተግባር ለዚህ ማስረጃ ነው:: መንግሥቱ ከኢጣሊያን ነጋዴዎች ጋር በመስማማት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የምዕራብ ሴቶች አለባበስ ቄንጥ ትርኢት እንዲደረግ ፈቀደ ይባላል::

ይህ አድራጎት በማናቸውም ረገድ ሊወገዝ የሚገባው ትልቅ ድፍረት ነው:: ምንም እንኳ በጎ ነገር መስሉ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ቡራኬ ተቀብሉ ቢቀርብም ትርኢቱ በቀጥታ የሕዝቡን ሞራል ለማጉደፍና ኢትዮጵያን የምዕራባውያን ብልጭልጭ ዕቃ ማራገፊያ ገበያ ሊያደርጋት የታቀደ ነው::የሥጋ ፍትወትንና ምቅንዝርናን ምኞት እንዲቀሰቅሱ ታቅደው የተቀደዱ የምዕራብ ሴቶችን ቀሚሶች ኢትዮጵያውያት እንዲለብሱ መፈተን ያገርን ባህል በጎ ቀርስ ለማውደም የታሰበ ዘዴ ነው::የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘመናዊ ቴክኖሎጂካዊ ጥበብን ለመቅስም ዝግጁነቱ የማይካድ ቢሆንም የምዕራባውያን የሞራል መበስበስ ያስከተለው የሥልጣኔ ፍግ መጣያ ለመሆን ከቶ ምኞቱ አይደለም::

ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ምክንያት በላይ በሳባታዊው የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ይህ አስጠያፊ ትርኢት እንዲደረግ መፍቀዱ ለጊዜው በገሩ ውስጥ የሚፈጸማቸው ያረመኔ ተግባሮች እንዳይታወቁበትና ከብዝበዛው የተነሣ ዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድህነት ከድንቁርናና ከበሽታ ተቆራኝቶ የሚኖር መሆኑን ለመሸሸግ የተሠራ የጭስ መጋረጃ ነው::እንዲሁም ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመሻረክ ብሔራዊ ማጋጣነት በመፍጠር የኢትዮጵያን ሕዝብ የባሕል መሠረት አፍርሶ ለመሄድ ያቀደው ማታለያ የተንኮል መሣርያ መሆኑ አይካድም::ነገር ግን የኢ

ትዮጵያ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ወንድሞቻችን በሚያስገርም የጀብዱ ተግባር የታቀደውን ተንኮል በገሃዱ በማጋለጥና ድምጥማጡን በማጥፋት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን እውነተኛ የመዘረፍና የጭቆና ሁኔታ ለዓለም ሕዝብ አስይተዋል፡፡መንግሥቱ ከቢረኞች ከኢምፔሪያሊስት ጋር በመሸረከ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በሚፈጽመው ግፍ አጥብቀው በመቆርቆር የአሜሪካኖችን ኢምፔሪያሊስቶች የበላይ የፕሮፓጋንዳና የባሕል መወቆና ቤት በመደብደባቸው የግንባር ቀደምትነት ተግባራቸውን በሚገባ ፈጽመዋል፡፡እኛ በአውሮፓ የምንገኝ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሁሉ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ያከናወኑትን የነጻነት ትግል በሙሉ የምንደግፍ መሆናችንን አንገልጻለን፡፡

በኢትዮጵያ አድማስ ላይ የነጻነት ጎሕ ቀደአል፡፡ፀሐዩ እንዳይወጣ ሊያግደው የሚችል ኃይል ከቶ በምድር ሊኖር አይችልም፡፡የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ይህን የታሪክ ግሥጋሴ ለመሰንከል በመሞከሩ ነው ዩኒቨርሲቲውን መዝጋቱ፡ ተማሪዎችን ማሰሩ፡ ከባሳባት ጭቆና ለመውጣት የሚታገሉትን የኢትዮጵያን ልጆች በተለመደው ያረመኔ ኃይሉ መፍጀቱ፡፡ነገር ግን ወደፊት ተራማጅ ኃይሎች ድል ይነሣሉ፡ አድሃሪ ኃይሎች እንደትቢያ ይጠፋሉ፡ ባሳባታዊው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥትና የበላይ ጠባቂው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ይሸነፋሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለዘለዓለም ይኑር!
የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ይኑር!

አዘጋጁ

## በኢትዮጵያ የሐሳብ ነጻነትና የጋዜጦች ሁኔታ

የሱፍ ሐበን

በኢትዮጵያ የሐሳብና የጋዜጣ ነጻነትን 'በንጉሥ ነገሥታዊ መልካም ቸርነት'ከተመለፀወትን እነዚህ አስራ በስት ዓመት መሆኑ ነው፡፡[1] እስካሁን ድረስ ግን ይህ 'ማንም በይጠይቅ በመልካም ፈቃዱ ደግነት የተሰጠ' ነጻነት ከብጫሽ ወረቀትና ከፕሮፓጋንዳ አልፎ ሥራ ላይ አለመዋሉን የሚጠራጠር አለ ብሎ ለማመን አስቸጋሪ ነው፡፡ ምናልባት እንዳንዱ አበሳባይ ቢሮክራቶች ተስኗቸው ሆነ ወይም አያውቁ 'ዘሬ እኮ እንደቱር አይደለም፡ በጋዜጣ በሬዲዮ እንዲያውም በቴሌቪሺን የፈለከውን ለመናገር ትችላለህ፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣንን አስከሚኒስትር ድረስ በመንቀፍ ነጻ ሐሳብህን ለመግለጽ ትችላለህ፡'እያሉ ቢያልፉ ቢያገድሙ ቢያወኩ ይታያሉ፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን መሠረታዊ ነጻነቱን እንደ መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች የተነጠቀና የተቀማ መሆኑን በሚከተሉት ገጾች ለማስረዳት እንሞክራለን፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ ጋዜጦችና በጠቅላላው የሐሳብ መግለጫዎች ሁሉ በበሳባታዊው መንግሥት እጅ ተከማችተዋል፡፡[2] ከዚህ መንግሥት የመጣ

---

1 የ1948 ሕገመንግሥት አንቀጽ 41 'በመላው የንጉሥ ነገሥት ግዛት ውስጥ በሕግ መሠረት የንግግርና የጋዜጣ ነጻነት የተፈቀደ ነው፡፡

2 ሆኖም ብስራተ ወንጌል ወይም በእንግሊዝኛ THE VOICE OF THE GOSPEL የሚባለው በዓለም ሉተራን ሚሽን የሚካሄደው ትልቅ ሬዲዮ ጣቢያ አለ፡፡ ይህ ጣቢያ በበሳባታዊው መንግሥት ቁጥጥር ሥር ከመሆኑም በላይ ነጻ ሐሳብ የሚገለጽበት መሣርያ አይደለም፡፡ ስለኒዎኮሎኒያሊዝምና ለኢምፔሪያሊዝም ማስፋፊያና ማጠንከሪያ አድሃሪውያን መንግሥታትን እንደኢትዮጵያ ያሉትን ባሳባታዊ መንግሥታት መደገፊያ ቀና መሣሪያ ነው፡፡ አረመኔው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በአፍሪቃና በኢትዮጵያ ላይ ሥልጣኑን የሚዘረጋበትና ሕዝቡን የሚበዘብዝበት ከጦሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ወይም እርሱ የማይቆጣጠረው ነጻ የሕዝብ መገናኛ ጋዜጣ ወይም ሌላ ነገር የለም፡፡ ማንም የግል ሰው ወይም ማህበር እነዚህን ሕዝብ መገናኛዎች ለማ ቋም አይችልም፡፡

በእደዚህ ባሉት የበሳበታዊ መንግሥት ጋዜጦችና ሌሎች የሕዝብ መገ ለጫዎች ነጻ ሕዝብ ለመግለጥ አይቻልም፡፡ 'ሳንሱር ወይም ሴንሰር' ሕዝብን መቆጣጠርና መመርመር፡ የማይስማሙትን እየነጠሉ ማስቀረት ስላለ፡ በሳበ ታዊውን መንግሥት የሚነቀፍ ወይም የሚቃወም ሕዝብ ሁሉ በጋዜጣ ወይም በሬ ዲዮ ሊነገር አይችልም፡፡ እንዲያውም ማንም ሰው እንደሚያውቀው ጋዜጦችና ጠቅላላው ፕሬስ አጼ ኃይለ ሥላሴን ለማወደስና ለማሞገስ የቆሙ ናቸው፡፡ እንዳንዱ እንደአጋጣሚ በእጃችን የገቡትን ጋዜጦች ይዘት — በውስጣቸው የተጻፉትን አርዕስት— በመዘርዘርና በመተንተን አሁን ከዚህ በላይ የሰነ ዘርናቸውን ሕሰቦች እርግጠኛነት ለማሳየት እንሞክራለን፡፡

1 የኢትዮጵያ ድምጽ 9–5–60 ዕለታዊ

ይዘት፡—

- ጃንሆይ የምድር በጦር ጉብኚ አበሉችን አነጋገሩ፡፡
- ጃንሆይ ቴሌግራም ላኩ፡፡
- ጃንሆይ በመሠረት ላይ ያለውን የመሐንዲስ ኮሌጅ ሕንጻ ጎበኙ፡፡
- የይመስቀል ለሆስፒታሎች የደም እርዳታ ሰጠ፡፡
- ቮለያ ንጉሤ ለሾፈሮች የ4 ቀን የትራፊክ ትምህርት ሰጠ፡፡
- $1600000 የሚፈጀው የምግብ ድርጅት ሥራ ሊጀመር ነው፡፡
- ከጋርሳማ
- ደቡብ ቬየትናምና የመን የፈርጅቀ እርዳታ ተነፈጋቸው፡፡
- ዶክተር ፔኒንግተን በኢትዮጵያ ያለም ጤና ድርጅት እንደራሴ ሆኑ፡፡
- በሽታ ባይኖር ርዕስ አንቀጽ
- ደብዳቤዎች 3
- ማስታወቂያዎች ጋብሊሲቲና የፍርድ ጉዳዮች
- የቦች ወረዳ ሕዝብ በ$12350 ት ቤትና መ ቤት አሠራ፡፡
- የደብረ ዘይት ንግድ ባንክ $639595 አበደረ
- የሬደል ሠራዊት የመጽሐፍ ስጦታ አደረገ፡፡
- የመንበረ መንግሥት ቀዳስ ገብርኤል መንገድ በሕዝብ ተሠራ፡፡



- 184773 ሰዎች ነጻ ሕክምና አገኙ፡፡ 'የሕክምና ክፍሉ ይህን አገልግሎት ያበረከተው በድንገተኛ ሕመም በያደበበዋና በየአብያተ ክርስቲያኑ ቀጥር ገቢ ወደቀው የተገኙትን ነው፡፡
- በአዲስ አበባ 32 አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ፡፡
- የጋብቻ ውል፡፡
- ዜና ዕረፍት

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት አርዕስት ውስጥ —ከጠቅላላው የጋዜጣው ይዘት— ከልቅምታሚና ትርኪምርኪ ተራ ወሬዎች በስተቀር ምንም ዓይነት ፍሬ ሕዝብ ያለው ጽሑፍ የለም፡፡ አብዛኛውን ቦታ የያዙት የአጼ ኃይለ ሥላሴ ዕለታዊ ገድልና ማስታወቂያዎች ሲሆኑ፡ ከአርዕስት ውስጥ አብዛኛች ከገራና ቀኝ የተያረመ መሠረታዊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ኑሮ ሁኔታ የማይመለከቱ ተራ ወሬዎች ናቸው፡፡

'በደብዳቤዎች'ዓምዱ ውስጥ ሰስት ነገሮች ተመልክተዋል፡፡ አንደኛው አንዱ ሰው በሕመም ምክንያት መንገዱ ዳር ወድቆ ባለ አንዱ ባለመኪና አን ስቶ ከቤቱ ስለወሰደው ባለደግ ተገበሩ በይፋ ይመስገን በማለት አንዱ ተመ ልካች የጻፈው ነው፡፡ ሁለተኛው ነጋዴዎች 'አምቦ ውሀ'መጠጥ ጨምረው ለማ ይጅዙ ሰዎች አንገሽጥም ብለዋል ቅብሉ ስለተጻፈ፡ ነጋዴዎችን አስታውቀን ብሉ 'የብሔራዊ ሀብት ልማት አክሲዮን ማህበር'የሰጠው መልስ ነው፡፡ ሰስ ተኛው 'ካርታ ካለው የከተማ ቦታ በስተቀር፡ የባለገር ርስት በምንም ዓይ ነት ለቀስትና አንቀበልም የሚሉ ባንኮች አሉ'ለ ተባለው የርስት አስይዞ ገ ንዘብ መበደር ጉዳይ 'እኛ አንቀበላለን' የሚል መልስ ነው፡፡

እንደሚታየው ከተራ ነገር መስመር የወጣ ምንም ዓይነት የሕዝብ ነጻነትን የሚያመለክተን ጽሑፍ አይታይም፡፡ 'በሽታ ባይኖር' የሚለው ርዕ ሰ አንቀጽም ርቀት ወይም ጥልቀት የሌለው ምስኪን ፍልስፍና ከገለጸ በኋላ በኢትዮጵያ ስለጤና አጠባበቅ እንደሚከተለው ይሰነዝራል፡፡ 'ሕክምና ሥራ ከቀድሞ የተሻለ ቢሆንም የሕዝቡን ፍላጎት ፈጽሞ አላረካም፡፡ በቂ ሐኪም

ችና ሆስፒታሎች ስለሌሉ በሽታ ለጊዜው ሊወገዱ አልቻለም:: ሆኖም በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ ይህ ጎልቶ የሚታየው ችግር እንደሚቃለል ተስፋ አለን::'

ይኸው ርዕሰ አንቀጽ ዛሬ ሕዝባችንን ስለሚጨፈጭፈው ኢንፍሉዌንዛ የሚባል በሽታ እንደሚከተለው ወሳኞይ አገም ጠገም አስተያየቱን ይሰጣል:: ሰሞኑን ዙሪያቸው በርከት ያሉ ሰዎች በኢንፍሉዌንዛ በሽታ ተበክለዋል:: ኢንፍሉዌንዛ ከየት መጣ? በብርዱ ምክንያት ነው? ከአየር ነው? ወይስ ከንጽሕና ጉድለት? የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስለኢንፍሉዌንዛው አመጣጥና መከላከያ ለሕዝቡ የሰጠው መግለጫ ባለመኖሩ በሽታው ስር እየሰደደ በመሄዱ ላይ ነው:: ከየፋርማሲው አስፕሮ ገዝቶ ከመቃወም በስተቀር ተገቢውን መከላከያ ሕዝቡ ቢያገኝ መልካም ነበር:: ኢንፍሉዌንዛ ተላላፊ በሽታ መሆኑ አልቀረም:: ሕዝቡ በሙሉ በዚህ በሽታ ከተበከለ ሥራውን ማን ያንቀሳቅሰዋል? በሽታ ባይኖር ዓለም ምች የመኖርያ ስፍራ በሆነች ነበር:: ፀታመና ሞትም ከበሽታው ጋር በጠፉ ነበር:: ዱሉትና ምቾት የሚመጣው ከሙሉ ጤንነት ነው:: የሰዎች ዕድሜ እንዲረዝም ከተፈለገ በሽታን ማውደም ያስፈልጋል:: ሌሎች ቀደም ብለው በሽታን ስላጠፉ በአገራችንም እንደዚሁ ዓይነት ሙከራ ማድረግ አያዳግትም:: ጊዜንና ወጪን ይጠይቃል:: ከሕይወትም የበለጠ ስለሌለ በሽታን ለማጥፋት መተባበር ያስፈልጋል::'

በመሠረቱ እንደዚህ ያለ አስተያየትና አስተሳሰብ ሬፎርሚስት መሆኑ ግልፅ ነው:: 'በጠቅላላው እስካሁን ደህና ተሠርቷል: ችግሩ በይወገዱ የመንግሥቱ ፖሊሲ ጉድለት አይደለም:: ሆኖም ጥቃቅን ጉድለቶች ካንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አይታጡምና ቢቻላችሁ አሻሽሉ::' የሚል ደንበኛ ሪፎርሚስት ነው:: ይኸውም ማለት የአሁኑ በሳበታዊ በላባታዊ አገዛዝን የተቀበለ፤ ነገር ግን ቀስበቀስ ይሻሻል: ወደከፒታሳዊ አቋም ይለወጥአል ብሎ የሚያምንና በዚሁ መንገድ ለመሥራት የታጠቀ



ነው:: እንደዚህ ዓይነት ሪፎርሚስቶች ከአሁኑ አገዛዝ ጋር የተዋሩት እውነትስ ዛሬ ኢትዮጵያን የገጠማት መሠረታዊ ችግር በሪፎርም ለመፈታት መቻል አለመቻሉን በእርግጥ አምነውበት ሳይሆን፤ የግዛ ራሳቸውን ጥቅም በበለጠ አቧጌን ለመጠበቅ በማለት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ —ጭሰኛው ገበሬውና ሠራተኛው— ከሚሠቃይበት ከድንቁርና የረሃብና የበሽታ ቢሎል በሪፎርሚዝም ለመውጣት እንደማይችል እስካሁን ድረስ በተደረገው የሥራ ውጤት —ያለፉትን የሃያአምስት ዓመታት የጠቅላላ ልማት ሁኔታ በኑሮ ደረጃ አድገት በጤና ጥበቃ በትምህርት ወዘተ. በመመልከት— ሳይረዱት ቀርተው ሳይሆን የአሁኑ አገዛዝ ጥቅም ተካፋይነታቸውን እንደያዙ የወደፊት እርምጃዎች ደጋፊዎች ወይም 'ፕሮግረሲቭ መስለው' መስለው ለመታየት የሚያደርጉት ጥረት ነው::

የዚህን ጋዜጣ በሪፎርሚዝም መንገድ ለማጭበርበር ለማሳሳትና ለማስመሰል መፍጨርጨር በጉልህ የሚያሳይ በ10–5–60 'ሳይሠሩ ማማት' በሚለው ርዕስ አንቀጽ ውስጥ የተሰነዘረው ሐሳብ ነው:: ሪፎርሚስቶ ጋዜጣ ከመሥመሩ ያለመጠን ወጥቶ፤ አለመኖሩን ዓለም የሚያውቀውን ነገር አለ ብሎ በመቀበል፤ በአሁኑ ባላባታዊ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል ምንም ዓይነት እምነት የሌላቸውን ውስጥ ውስጡን የሚያሽሟጥጡትን የሚሰለቁበትን የሚነቅፉትን ምሁራን —ኢንቴሌክቿልስ— በማበጣት ይወርዱባቸዋል:: የሐሳብና የጋዜጣ ነጻነት እንደሌለ ሥራ ላይ እንዳልዋለና እንደማይውል ማንም ያውቀው ነገር ቢሆን፤ ሪፎርሚስቶ አዘጋጅ ግን 'አለ፤ ጋዜጣው ፕሬሱ ሁሉ ነጻ ነው፤ እናንተ ስንፎች ምሁራን፤ ሐሚታችሁንና ማሽሟጠጣችሁን ትታችሁ ለምን ነጻ ሐሳባችሁን አትገልጹበትም?' በማለት እንደሚከተለው ያሰባል::

'በአሁኑ ጊዜ ጋዜጠቻችንና ራዲዎውም ለሕዝብ የሚሰጡት አገልግሎት የተጠበቀውን ያህል አይደለም የሚል ስሞታ አልፎ አልፎ ይሰማል::በመሠ

ረቀ ረቂቅ ቴሌቪዥንና ጋዜጠኞች ከአሁኑ የበለጠ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል
የሚለውን አስተያየት እንቀበለዋለን:: — — — ምናልባት አገልግሎታቸው
በደሚሳ የርቷል ቢባልም ከውጭ —ከሕዝብ— የሚሰጣቸው ዕርዳታ በጣም አነ
ስተኛ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል:: የጋዜጣ አንባቢያን እንደሚያውቁት
ሁሉ በከፍተኛ ትምህርት ከበለጸጉት ወጣቶች መካከል ለጋዜጣ ጽሑፍ የሚ
ልኩት በጣም ጥቂቶች ናቸው::ሕዝብን ለማስተማርና ለመምከር ፕሬስ ዓይነ
ተኛ መሣርያ መሆኑን ቢያውቁ የርተው አይደለም:: ዕውቀታቸውን በፕሬስ
አማካይነት ሳስተማሩቸው ሕዝብ ማበርከት ቢችሉ ከዓር የሙው የሚያሸሟጥ
ጠበት ምክንያት አይገበንም:: ሸሙጥና ጤሚት የሚያሸሽለው አንዳችም ነገ
ር አሰሙኖሩን መገንዘብ ይኖርብቻዋል::

የሐሳብና የጋዜጣ ነጻነት የሰው ልጅ መሠረታዊ መብት የሆነው
ዘሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አርበትና ተነፍገት በለበት ጊዜ 'ከማሽሟጠጥና
ከማማት ሌላ ምን ጽሑፍ አታበረክቱም?' ብሎ እንደዚህ መጠፈር ነገሩን ሰያ
ውቀ በይሆን ደህና አድርጎ በመረዳት ከዚህም ከዚያም በማለት የራስን ጥ
ቅም ከፍ ለማድረግ የተሰነዘረ ከንቱ መወናበዱ ነው::ከቡር የጋዜጣው
አዘጋጅ የረከሰውን የሚኒስትርነት ማዕርግ ለማግኘት የሌለውን አለ ብሎ
ማጭበርበር በምክር በርሶ የተጀመረ ባይሆን እንኳን በዚህ ሁሉም በሚ
ያውቀው ነገር [redacted] እንደዚህ ያለ ድፍረት ማድረጉ ከቀናት ከገብር ብጫ
ዎች በበለጠ ሊያጋልጠው ይችላል::

አሁን ባለንበት ወቅት ያገሬችን መሠረታዊ ፕሮብሌም በመሠረታዊ
ለውጥ መሠረታዊ መፍትሔ ማግኘት ይገባቸል፤ በማለት ከሚታገሉት ተሰብኢያ
ዊ የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የኀንበር ቀደ
ምነትን ደጀን ይዘው የሚገኙ መሆናቸው ለማንም ያልተሰወረ ነገር ነው::
ሆኖም እነዚህ'ሳይሠሩ የሚያሙ ሰነፎች'ከትግሉ አፍላ ውስጥ የገቡትን
ረብሻሽነኞች ሳይሆን በአሁኑ አገዛዝ አስተዳደር ውስጥ ተሰግስገው ሠሬተ



ኛውንና ገበሬውን ሕዝብ የሚመጥጡትን የተወናበዱና ሬፍርሚስት ቢሮክራቶች
የሚመለከት በይሆን አይተርም:: የበሳበታዊው መንግሥት ፕሬስ ሲያትም የሚ
ቾለው የሪፍርሚስቶችን የተሸናፊዎችን —ሊሬቲስትስ— የአበሳብዮችን —ኦፖር
ቹኒስትስ— በጭሩ ያወዳሸችን ጽሑፍና አስተያየት ነው እንጂ የሪቪሊሲስቶ
ችን አይደለም:: በጁምሳ ሁሉንም በእንዱ መስመር ከማስገባት ሁሉንም ለያ
ይቶ በሰሙ መጥራት የተሸለ ነበር::

2 — እንደዚሁ በጋጣዊ የ16—5—60 'አዲስ ዘመን' ይዞት የተ
መለከትን እንደሆነ፤ በርዕስ አንቀጹና አንዳንዱ ደብዳቤዎች በስተቀር ሌላው
ከወዲያ ከወዲህ የተለቀመ ተራ ንጉሣዊ ወሬ ብቻ ነው:: ሪፍርሚስት ቢሆንም
ምንም አይነት ሰሬ ሐሳብ የሚገልጽ አምዱ የለውም::

የደብዳቤዎች አምዱ በሰምነት እንዱ ቀን ስለኢንዱስትሪ፤ነንዱ፤ቀ
ጠብ፤ የማስታወቂያና የንግዱ ሚኒስቴሮች በመተባበር ከሕዝብ ለቀረበላቸው
ደብዳቤ ጥያቄ የሚያቀበረብር መልስ የሚሰጡበት ገጽ ነው:: ይኸውም አን
ል አበታዊ ምክር የሚሰጥበት አምዱ ማለት ነው:: ውስጡ ምን እንደሆነ
ለማስረዳት የሚከተለውን ጥያቄና መልስ ከዚህ በላይ ከተመለከተው ጋዜጣ
ውስጥ እንጠቅሰዋለን::

'አዘጋጅ ሆይ፤ የንግዱ ሚኒስቴር ኢንስፔክተር: ነጋዴዎችን ለመ
ቆጣጠር ባለፈው ነሐሴና መስከረም ወሮች መጥቶ የዕቃዎችን ዋጋ አስተካክሉ
ብሎ ሄደ ነበር:: ነገር ግን እርሱ በሄደ በስት ቀናት በማይበልጥ ጊዜ
ውስጥ ነጋዴዎች እንደፈለጉት መሸጥ ጀመሩ:: እኛም እርሱ ያወጣውን ማስታ
ወቂያ አንብበን ለምን ከተወሰነው ዋጋ በላይ ትሸጣላችሁ? ብለን ብንጠይ
ቃቸው፤ ምን አገባችሁ? ብትፈልጉ ግዙ ብትፈልጉ ተውት አሉን:: እንግዲ
ህ እንደዚህ የመሰሉቱትን ሕገወጥ ነጋዴዎች እንዴት ለማድረግ ይሻላል? አስ
ተያየትዎን እንጠብቃለን::' በርሄና አበተ ከአዱቀ ከተማ::

<u>የመንግሥቱ ባለሥልጣን መልስ</u>፡ 'ተቆጣጣሪው ያሉትን ያለመፈጸም በነጋዴዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የሚገፋፋ ነው፡፡ ብዙዎች የወጣውን ማስጠንቀቂያ አክብረው እንደተባሉት ቢፈጽሙ የአዱቀዎች ያለመተባበር የሚያባዝን ነው፡፡ አሁንም ሁኔታውን ተከታትለን ትክክለኛውን መንገድ ለመያዝ እንዲቻል የተባሉትን ነጋዴዎች ስም ዝርዝር ከነአድራሻቸው ለወኪላችን ቢሰጡዋቸው ወይም ቢልኩልን መልካም ነው፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ንግድ የሚካሄደው በነጻ ውድድር ስለሆነ፣ ከመወንጀል አስቀድሞ ነጋዴዎች ሕጉን መጣስ አለመጣሳቸውን አስቀድሞ ማጣራት ይሻላል፡፡'

በዘራፊዎች ነጋዴዎች ዘጠቀኖ መድረሻ ሳጣው ሕዝብ እንዲህ የሚሰጠው መልስ እንደዚህ ያለ ነው፡፡ ጥራው የማይጠበቅ ራስና አገሩ ተለይቶ የማይያዝ እንዲያውም ለይስሙላ ሕዝቡን ለማታለል የተሰነዘረ ተንኮል መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ እነዚህ የተቸገሩ ዜጎች ነጋዴዎችን ከሰው ለማስቀጣት እንደማይችሉ፡ ወይም ዋጋው በጣም ትልቅ መሆኑን ስለሚያውቁት ምንም ዓይነት ሙከራ አያደርጉም፡፡ መልስ ሰጭውም የባላባታዊው መንግሥት ሉሊ ስለሆነና ነጋዴዎች ደግሞ የዚሁ አድሃሪ መንግሥት ደጋፊዎች በመሆናቸው ምንም ዓይነት ቅጣት እንደማይመጣባቸው ያውቃሉ፡፡ ሕዝቡ ወዲያ ወዲህ እንደተቀከበ የሚይዘውንና የሚለቀውን አጥቶ መሰቃየቱን ይቀጥላል፡፡ ባላባታዊው መንግሥት በሕዝቡ ላይ የሚጫወተው ትራጂ--ኮሚዲ መሆኑ ጉልህ ነው፡፡

መሠረተ ሐሳብ የሌለው 'የሠራተኞች ማህበር' የሚለው ርዕስ አንቀጽ የባላባታዊውን መንግሥት ጥቅም ጠባቂነቱን የሚገልጸው ለመብታቸው የሚታገሉትን ሠራተኞች በመዝለፍ ነው፡፡ ዋናው አማካይ ማህበር ከኢምፔሪያሊዊ ሠራተኞች ማህበር የተመጸወተውን ረድኤት ካመለከተ በኋላ እንዲህ ይላል፡፡ 'ይህ ሆነ፡፡ ከድርጅቱ የጠበቅነውስ ከባዱ ኃላፊነት ያለው ተግባር ነው፡፡ የሥራው እንቅስቃሴ መታረፍ ያሸሪቱን ኢኮኖሚ እንዳይጎዳ ማሰብ ያለበት ነው፡፡ ማሰብ ብቻ ሳይሆን ኃላፊነቱን መሸከምም ማንበድዱም ይኖርበታል፡፡



ሁሉም መቀፍ ናቸው ባንልም፡ አልፎ አልፎ በሠራተኞች መካከል ተንኮለኞች አሉ፡፡ በኛ ብቻ አይደለም፡ በየትም ነው፡፡ ተንኮለኞች ተንኮላቸውን እንዳያጋቡ መከላከል ያለበት የሠራተኞች ድርጅት ነው፡፡'

ምንም እንኳን በባላባታዊው መንግሥት ሉሌዎች መካከል ምንም ዓይነቱ መሠረታዊ ልዩነት ለማድረግ ባይቻል፡ ይኸኛው 'ከጽምፀም' ወደቀኝ የሚገኝ ፍጹም አድሃሪ ክንበርሽ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በባላባታዊ አገዛዝ ፍልስፍና ተንጠርብቦ በመምሳቱ በተሰጠው መሣርያ ወደፊት ተራማጅ ኃይሎችን ለመጨፍጨፍ አይመለስም፡፡ ኃይለኛ ተናካሽ ውሻ መሆኑን በማየት ነው ባላባታዊው መንግሥት ይህን ..ቁርስ የተከለለት፡፡ ይህ የሻለው ቀርቡ አንድ ቀን የኢትዮጵያ ሠራተኛና ገበሬ በንዴት የተነሣ ዕለት ተሰብሮ እንደሚወድቅ አይመስለውም ይሆን?

3— 'ዘ ኢቲዮፒያን ሄረልድ' የሚባለው ዕለታዊ የእንግሊዝኛ ጋዜጣ በዚያ በወሳቀይ አበሳ በይ የሚዘጋጀው እንደቀፉት የባላባታዊውን መንግሥት እናት አወዳሽ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በ3—2—68 የወጣውን ቁጥር የተመለከትን እንደሆነ 'ዳንሆዬ የእስራኤልን የንግድ ኢኮኖሚ ሲዎን ከፈቱ፡ — — — ዳንሆዬ ይህን አደረጉ፡ ይህን ፈጠሩ' በሚል በአንዱ ሰው ከንቱ ውዳሴና አምልኮ የተበከለ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ሙሉ ጋዜጣው ከግራ ከቀኝ በተለያዩ ርካሽ ወሬዎች የተሞላ ስለሆነ እንደዚህ ባለ ሰፍራ እንኳን ነጻ ሐሳብ ሊናገር ይኖራል ብሎ ሊታሰብም አይችልም፡፡

4— በነደቀ ዓሳማችን የሚለው በሞናዊ የባላባታዊው መንግሥት ጋዜጣ መሆኑ ነው፡፡ በ25—5—6፬ የወጣውን የተመለከትን እንደሆነ አብዛኛውን ስፍራ ይዞ የምናገኘው ስለአጼ ኃይለ ሥላሴና ስለፕሬዚዳንት ቲቶ የተጻፈ ወሬ ነው፡፡ እነዚህ አዛውንት የተለዋወጡት ነገሮች —ዲስኩሮች— እንደዚሁም የፈጸሙዋቸው ነገሮች በጣም ጎልተው ተጋነው ተጽፈዋል፡፡ የቀ

ረው አበዛኛው አዳቀሩት የበሳበታዊው መንግሥት ጋዜጣዎች በትርኬሞርኪ የተ
ቀሳ ነው:: 'ሰይፃጠል በቀጠል' የሚለው ርዕስ አንቀጹም ስለዓሉም ወርነት
ና በሰም ሁኔታ ቀበቻሪ ትችት ነው::

'አዲሱ ኢትዮጵያነት' የሚለው ርዕስ ስር 'ጋሳሬነት በገብር መታየ
ት አለበት የሚል ዓይዱ ከአቶ መዝገቡ አበተ ተዘጋጅቶ ታትሟል:: የበሰበ
ሰውን ቢሮክራሲ ለማስደንገጥ የተፃጣ ይመስላል:: በመጀመርያ ደራሲው በመ
ንግሥት መሥርያ ቤቶች ውስጥ የሚደረጉትን አንዳንዱ መጥፎ ልማዶች ያጋለጠ
ይመስላል:: 'እነዚህ ፈላጦች ተመርኩዘው የመንግሥት መሥርያ ቤቶችና ድር
ጅቶችም በአንዱ ዓይነት ልምዱ የታሰሩ ቢኖሩ፡ ጊዜው ያለፈበት ድርጊት
ነው አንገሳቸቀለን:: ጊዜያችን የገል ጥቅምን በመፈለግና ወገንና የቀርብ ወ
ዳጅን በመጥቀም ያስቸሉታ በማይቻለው የሥራ መደብ መደልደልን አይፈቅዱም::
ሌላው በጣም የሚጠላውና በዘመናዊው ትውልዱ ዘንዱ ተንገቀሎ የወደቀው ልማ
ዱ በንዳንዱ ስፍራ ገን ስር ስደ አልነቀል ብሉ ያስቸገረው፡ 'አቪ ነገ'
ነው:: እንደዚህ አያለ ከዚያው ባገኘው ስሬ ልምዱ አገሌ ነው በማይባሉ
ብጫዎች ቢሮክራቶች ሳይ ከተጋበዘባቸው በኋላ 'ወደ ቀኝ ዙር' በማለት
ዓብሩን ለማዱረስ ይችኩሳል::

'የኢትዮጵያ ሕዝብ ከበርና ነጻነት አስከዘረ በወገና በስርዓት ተጠ
በቀ የኖረው አንዱነታችንና መሠረታዊ ይዞታችን ነበር ታሪኩን ይዘ ወደፊት
በመሬመዱ የቆም ነገር ደሊት የሚያስኘውን ስም ያቀዳጀውን አመራር ጥሩ ፈለ
ጉን ባይለቀ ባለአደራዎች የባለአደራነታቸውን ዓብር በንጹህ በመቀጠላቸው
ስለሆነ፡ አሁንም በዚያው መሠረት እንዲቀጥሉ አበረሳገ መሆኑን አየደጋገምን
እናስታውሰቻቀለን::'

ጽሑፉመሠረት የሌለው ከተወናበደ አበሳበይ አንጎል ብቻ ሊመመንጨት
የሚችል ነው:: ምስኪን የሆኑ ሰማቸው ያልታወቀ ቢሮክራቶች በዚያም በዚህም



ተጎሽመቀል:: ባሳበታዊው መንግሥት በደህና እንደሚመራና የቆም ነገር ደቢ
ትም እንዳስኘን ተነገረናል:: ቢሮክራሲው የባሳበቶ መንግሥት ዓቶች ስለሆ
ነ እርሱን የነቀፉ አየመበሉ ባሳበታዊውን አገዛዝ ማመስገንና መከበ 'እህ
ያውን ፈርቶ ዓውሳውን' እንደሚባለው ምሰሌ ነው:: እንደዚህ ዓይነቶ ተያ
ራኒ ነገር የሚደረገው ስይታወቅ ባይሆን ጥቅምን ለመፈለግ ነው:: ባጭሩ
የሚለው 'ኢትዮጵያን በውጭ ደህና አድርገው ያበወቅዋትና ትልቅ ስም ያስ
ገኙላት በአገርም ውስጥ ለሕዝቡ ብዙ መበበል ያመጡለት እንደአባት የሚያስ
ቡለትና የሚሠፉለት አሌ ኃይለ ሥላሴ ናቸው:: ሕዝቡን የሚያጉላሉትና የሚ
ጠቀኑት የመንግሥት ባለሥልጣኖች ዲሬክተሮች ሚኒስትሮች እንዲሁም አገረ
ገዢዎች:: 'ይህ ዘዴ የአፄ ኃይለሥላሴ ዋና መመፈያ መሆኑ የታወቀ ስለሆነ
ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀበው አምዱ ብጫ በላይ የመጫ ትዕዛዝ ሊሆን ይች
ሳል:: ለማናቸውም ይህ ጽሑፍ የሐሰብና የጋዜጣ ነጻነት አለ ተብሎ ሲም
ስከርነት የሚቀርብ አይደለም::

5— ሁለተኛውን በሞናዊ ጋዜጣ 'የዘሬይቶ ኢትዮጵያ' የሚባለውን
የተመለከትን እንደሆነ 'ከዱምጽ' ወይም 'ከአዲስ ዘመን' የተሻለ ሆኖ አገደ
ማናገኘው ባይታሰም የተሬታ ነው:: እንደቀፉት የሕዝብ ጨሳት የሆነው የበ
ሳበታዊ አገዛዙ መሣርያ ነው:: እንዳጋጣሚ እኛችን ውስጥ የዐደቀውን የ2—
6—60 ቀጥር ይዘት አልፈን አልፈን የተመለከትነው እንደሆነ 'ገርማዊ ገ
ንሠ ነገሥት በአሥመራ የሚያደርጉትን ጉብኝት ቀቀሰቀል፡ የአውራ ጎዳና
ባለሥልጣኖች መንገዶችን ለምክር ቤት አባሎች አስጎበኙ፡ በበረና አውራጃ
52 የዘሳን ማበረፊያ ጨቢያዎች ተቋቋመቀል፡ የቪየትናም ጦርነት መልኩን
ለውጧል ይባላል፡ ወዘተ:: 'ከነደዚህ ያለ ተራ ወሬዎች በስቀረ አርባን
ያለው ነገር የለበትም::

'የተፈጠነ ዕዉገት' የሚለው ረዕስ አንቀጽ ያልተሠራውን ተሠራ፡ ትገ

ሙን ትልቅ አድርጎ በሳበታዊውን መንግሥት የሚያወድሱና የሚያኳሽ ሕዝቡን የሚያታልል መሆኑን በንዓንድ ተቀቦች እናሳያለን፡፡ 'ኢትዮጵያ ዛሬ ብሩህ የሆነ ዕድል ይጠብቃታል፡፡ የምትራመደው ወደ ብልጽግና ነው፡፡' ብሉ ሕልሙን ከአወሬ በኋላ 'ኢትዮጵያ ዛሬ በተቻለ ፍጥነት ወደፊት ከሚራመዱት አገሮች አንዷ ናት፡፡ ይህም የአገሪቱ እርምጃ በግርማዊ ጃንሆይ ከፍተኛ መሪነ ትና በርቱ ጥረት የተገኘ ፍሬ ነው፡፡' በማለት ገብሩን ያደርብል፡፡

በርዕስ አንቀጹ ውስጥ የአዲገ ኤርትራ ዝብኘት ሲቀብብ፡ በዚህ ክፍለ አገር ውስጥ የኤኮኖሚ ችግር ያስከተለውን መሠርያዊ ትግል እንዳልነበረ እንደሌለ በመቀጠር 'በዚህም በሥነት ገርማዊ ጃንሆይ የኤርትራን ጠቅላይ ገዛት በመጎብኘት፡የተፈጸሙትን የልማት ሥራዎች በመመረቅ፡ወደፊት የሚሠሩትን የመሠረት ድንጋይ በማኖር ላይ ናቸው፡፡ የኤርትራ ጠቅላይ ገዛት ሕዝብ ከጥንታዊ አካሉ ከኢትዮጵያ ከተቀሃደበት ጊዜ ጀምሮ ኑሮው እየተሻሻለ ሂዷል፡፡ በመቶ የሚቆጠሩ ኢንዱስትሪዎች ተቋቁመውለታል፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ በዚህ በፊት ከነበሩት አሥር ዓመታት ከተሠራው ከእጥፍ በላይ የልማቱ እድገት እንደጠመረ ታውቋል፡፡' ብሉ በአሁኑ ሁኔታ ሲደሰል የማይችለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለል አስቧል፡፡ ነገር ግን ከንቱ ጥረት ነው፡፡

ይህ ጋዜጣ ምንም እንኳ የሐሳብ ነጻነት በለመኖሩ ባሳባታዊውን አገዛዝ የሚቃወም ጽሑፍ ስፍርበት ባያውቅም፡ ከበፊት ጊዜው አሁን እየባሰ መሄዱን ለሚያውቁት አንባቢዎች ሊሰወር አይችልም፡፡ በፊት ጊዜ በመጠኑ አንዓንዱ ትንሽ ሻል ያሉ ሪፎርማዊ ሐሳብ የያዙ አምዶች ይወጡበት ነበር፡፡ዛሬ ዛሬ አልም ብሉ ረከቦ የአዲ አወዓሽ ሆኗል፡፡ በዚህ ስምናዊ ጋዜጣ እዚህ ገባ የሚባል ትንሽ ሻል ያለ ሐሳብ ያለበት አንዱም አምዱ አይታይበትም፡፡ ይኸውም አንዓንዱ አበሳ ባይ ቢሮክራቶች እንደሚወሸክቱት የሐሳብና የጋዜጣ ነጻነት እየተሻሻለ ሂደ ማለት ባይሆን እንዲያውም እየባሰበት ወደታች መሄዱን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡



በኢትዮጵያ አንገሪ የሐሳብና የጋዜጣ ነጻነት አለ ወይስ የለም? የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን መሠረታዊ ሰብአዊ መብቱን ተገፍሎል ወይስ አልተገፈፈም? ከዚህ በላይ በተደረገው አጭር ትንተና ጥናት እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አያስቸግርም፡፡ ሪቮሉሽናዊ ኢትዮጵያውያን አስቀድመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር በንዴት ያለ መንገድ መፈታት እንደሚችል አጠናውቀው ስለሚያውቁ መልባቸውን ከስው የይቀዋል፡፡ ነገር ግን አንዓንዱ ቢሮክራቶች ወይም ተማሩ ከተባሉት መካከል ብዙውን ጊዜ አያወቁ ሕዝብን ለማታለል የሐሳብና የጋዜጣ ነጻነት አለ የሚሉ አሉ፡፡ የአድሃሪውን ባሳባታዊ አገዛዝ ጋዜጣዎችና በጠቅላላው ፕሬሱን የሚመሩትና የሚያንቀሳቅሱት ቢሮክራቶች ቀና ቀያ አድርገው የያዙት ይህን የማስመሰልንና የማታለልን ዝቅተኛ ተግባር ነው፡፡ ከዓር ቀኝ አድሃሪዎያን አስከ መካከል ገሬ ሪፎርሚስቶች፡ በሃብትና በሥልጣን ከዓበሩት ኮንስርቫቲቮች በሁኑ አገዛዝ ስር አንዓንዱ መሻሻል ለማምጣት ይቻላል ብሉ እስከሚያምኑት ፕሮግረሲቭ ብጤዎች፡ በዚህ ረገዱ ተወናብደው ሕዝብን ለማወናበዱ እንደሚምክሩ የታወቀ ነገር ነው፡፡ ይኸውም ሊያስገርመን የማይችለው ባሳባታዊውን አገዛዝ ደግፈው የያዙት ቢሮክራቶች የቀኛ ሆኑ የገራ ጥቅማቸውን ከሕዝብ ይልቅ ከወደኋላ ተመልከቶ ባሳባታዊ መንግሥት ሕይወት ጋር ስላቆራኙት ነው፡፡ የእርሱ መውደም የእነርሱም ጥረት ስሉሆነ፡ ሕዝብን እየዘረፉና እየጨቆኑ እንዱነት ተደጋገፈው ለመኖር ይጥራሉ፡፡ ለሪቮሉሽነሮች የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወደቀበት የድንቁርና የበሽታና የረሃብ ኩነኔ ውስጥ ሉወጣና ብሔራዊና ሰብአዊ መብቶችን በሙሉ ሊቀዳጅ የሚችለው፡ የአሁኑ አድሃሪ አገዛዝ ከነግብረአበሮቹ ከኢትዮጵያ ምድር በጦር ኃይል ደምስስ ቢያጠፉቸው ብቻ ነው፡፡ በአሁኑ የዓለም ትግል ሁኔታ ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው፡፡

# የኤርትራ ሕዝብ ትግል

(ተገቢ አጀማመር ሕዝባዊ ያልሆነ አመራር)

**ወርደፋ ገመዳ**

'የኤርትራ ነጻነት ግንባር' በኤውሮፖ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማህበር ስበተኛ ጠቅላላ ጉባኤ አንድ መልእክት አስተላልፎ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ የዚህ መልእክት ዋናው ፍሬ ነገር ውይይት እንጀምር የሚል ነበር፡፡ መልእክቱ የደረሰው በጉባኤው ፍጻሜ ላይ ሲሆን ጉባኤው ግን አስቀድሞ ስለኤርትራ አንድ ውሳኔ አድርጎ ነበር፡፡ በውሳኔው ውስጥ ያውሮፖ ማህበር አድሃሪው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት መንግሥት በሰላማዊው ሕዝብ ላይ የሚያደርገውን የቦምብ ድብደባና ሌላም የግፍ ሥራ ሁሉ በጥብቅ እየተቃወመ አስፈጻሚው ኮሚቴ ስለግንባሩ የተጣራ ጥናት እንዲያቀርብ አስበወል፡፡

ዛሬ ባለንበት ወቅት የኤርትራ ጉዳይ ፖሊቲካዊ አስተያየት ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከሁለት ዋና ክፍሎች ከፍሎአቸዋል ለማለት ይቻላል፡፡ አንደኛው ክፍል ያሳነሳች ቅሬታ፡ የግንባሩን ፖሊቲካ እንጂ በተጣራ መልክ ሳይገነዘቡ፡ እንደዚሁ ብቻ በደፈናው አንቀበሉውን ይደግፋዋል፡፡ ሁለተኛው ወገን ደግሞ እንደዚሁ ያሳነሳች ቅሬታ ያድሃሪውን መንግሥት ፕሮፖጋንዳ ተከትሎ አንቀበሉውን በደፈናው በታላቅ ቅንዓት ይኮንነዋል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባለችው መሠረታዊ የግንኙነትና የጽሑፍ ነጻነት በሌለበት አገር ውይይትና ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ፡ ክርክርና ዲሞክራሲያዊ ውሳኔ ሊደረግ ስለማይቻል ሁለቱም ወገን የራሱን እምነት ለመሰሎቹ ካልሆነ ሌላ ባይገልጽ እርስበርሱ ቢጠረጠርና ቢተማማ እንዳለ ተቀምጧል፡፡ ይህ ቢሆን አድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት እንደለመደው በሰላማዊው ሕዝብ ላይ የሚከኔ ወንጀልን በመሥራት የኤርትራን ሕዝብ ትግል ለመደምሰስ ሙሉ ነጻነት አግኝቷል፡፡



በኔ አስተያየት የሁለቱም ወገኖች አስተሳሰብና እምነት የተመሠረተው በምርመራና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠቅላላ ሁኔታ በማጥናት ላይ ሳይሆን በስሜት ብቻ ላይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ መለወጥ አለበት፡፡ ስለኤርትራ ጉዳይ የተጣራና በምርመራ የተመረኮዘ ትክክለኛ አስተያየትና መመርያ ያስፈልገናል፡፡ የዚህን ዓይነት አስተያየት ለመፍጠር ደግሞ መወያየትና መከራከር ፍጹም ተፈላጊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንዳገኙ ሊያስቡና የክርክር መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ አስተያየቶችን ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡ ሁለቱም ወገኖችና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ከሁኑ ማሰላሰል እንደሚጀምሩና ሃሳባቸውን እንደሚገልጹ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

## 1. የኤርትራ ሕዝብ አጭር የቅርብ የፖሊቲካ ታሪክ

ምንም እንኳ የብዙ ሺህ ዘመናት የኤርትራ ሕዝብ ታሪክ በሙሉ ደገጿው እኒኒፉ ከቀረው ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚያገናኘውና የሚያመስስለው ቢሆንም፡ የኤርትራ ሕዝብ ካሥራ ዘጠነኛው ክፍለዘመን መጨረሻ ጀምሮ እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድረስ የኮሎኒያሊስቶችን ጭቆና ቀምሷል፡፡ ይህች የስድሳ ዓመት ታሪክ ከረጅም ዘመናት ታሪኩ ጋር ስትመዛዘን ትንሽ መስላ ብትታይም የኤርትራን ሕዝብ ከቀረው ኢትዮጵያ ነጥላው ምልክት አድርጋ በታለች፡፡ በተለይም ጠቋኞችን መታገያ ዘዴና ልምድ አስተምራቸዋለች፡፡ በኢጣሊያኖች ዘመን ሽፍታ እየተባለ ሲጨፈጨፍ የኖረው የኤርትራ ሕዝብ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የገፈኞችን ቀንበር አሜን ብሎ ተቀብሎት እንዳልነበረ አይጠረጠርም፡፡

ከስድሳ ዓመት ትግል በኋላ በ1935 —በዚህ ጽሑፍ የሠፈሩት ዓመታት ሁሉ በኢውሮፓ አቆጣጠር ነው— የኢጣሊያን ኢምፔሪያሊስቶች በኤርትራ በመጠቀም ኢትዮጵያን ወረዋታል፡፡ በ1941 ኢጣሊያኖች በኤርትራ ሲደመሰሱ እንግሊዞች በገሪቷ ላይ የወታደር አስተዳደር —ብሪቲሽ ሚሊተሪ አድሚኒስትሬሽን

አስፈፃበት::በኤርትራ የፖሊቲካ ታሪክ ውስጥ በ1941 እስከ ፌዴሬሽኑ ድረስ ያለውን ጊዜ በተለይ መመልከት ያስፈልጋል::

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አራቱ መንግሥታት ማለት የእንግሊዝ የፈረንሳይ የአሜሪካና የሶቭየት ሕብረት: የኢጣሊያን ቅኝ አገሮችን የወደ ፊት ዕድል አንድነት በስምምነት ሊወስኑ: በስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ግን ነገሩን ወደተባበሩት መንግሥታት ሊያስተላልፉ ውል ገብተው ነበር:: በዚህ አኳኋን በ1947 የኤርትራን ጉዳይ የሚያጠና ያራቱ መንግሥታት የምርመራ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ ተልኮ የሚከተለውን የፖሊቲካ ሁኔታ በገሪቷ ውስጥ አገኝቷል::በኢጣሊያኖችና ከክልሎች የፖሊቲካ ቡድኖችና ድርጅቶች ሌላ ስድስት ትልልቅ የኤርትራውያን የፖሊቲካ ቡድኖችና ድርጅቶች በገሩ ውስጥ ነበሩ:-

<u>1ኛ የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ያርበኞች ማህበር—ዩኒዮኒስት ፓርቲ</u> የተመሠረተው በ1941 ያባሎች ቁጥር 729000::ከአባሎቹ ሁለት ሶስተኛው ክርስቲያን የቀረው ብቻ እስላም ቢሆን በጠቅላላ 195000 የሚሆኑ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሌሎች አባሎች ነበሩ:: ፕሮግራሙ ያላንዳች መከፋፈል በቀጥታ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል ነበር::

<u>2ኛ የኤርትራ እስላሞች ማህበር —ኢሬትሪያን ሞዝሊም ሊግ—</u> የተመሠረተው በ1946 በሕግ የታወቀው በ1947 ያባሎች ቁጥር 732000:: አባሎቹ በሙሉ እስላሞች ቢሆኑ ብዙዎቹ ጭሰኞች ነበሩ::ፕሮግራሙም ሀ/ የኤርትራን ብሔራዊ አንድነት ማጽደቅ ለ/ ለኤርትራ ነጻነት መታገል: ነጻነት ካልተቻለ ግን ላሥር ዓመት ኢንተርናሽናላዊ ቁጥጥር ባለበት በእንግሊዝ ተጠባባቂነት ሥር መቆየት: ሐ/ ከሱዳንና ከኢትዮጵያ ወረዳዎች አንዳንዶች ለኤርትራ እንዲመለሱ ማድረግ: መ/ ከኢትዮጵያ ጋር የመቀላቀልን ሐሳብ በጥብቅ መቃወም: ሠ/ የእስላሞችን መብትና ጥቅም ማስከበር ረ/ የገበርነትንና የጭስኝነትን አስተዳደር ማቆረት::



<u>3ኛ ሊበራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲ</u>: የተመሠረተውና የጸደቀው በ1947: ያባሎች ቁጥር 53000: ሁሉም ክርስቲያን: ፕሮግራሙ ሀ/ የኤርትራን ብሔራዊ አንድነት ማጽደቅ: ለ/ በተባበሩት መንግሥታት አማካይነት ቀስ በቀስ የኤርትራን ነጻነት ማስገኘት ሐ/ ትግሬንና አንዳንድ የሱዳን ወረዳዎች ለኤርትራ እንዲመለሱ ማድረግ መ/ ከኢትዮጵያ ጋር የመቀላቀልን ሐሳብ በጥብቅ መቃወም::

<u>4ኛ ያዲቢቱ ኤርትራ ቡድን —የኢጣሊያኖች ወገን—</u>: የተመሠረተውና የጸደቀው በ1947: ያባሎች ቁጥር 219000: ክርስቲያንም እስላምም አሉበት:: ፕሮግራሙ ሀ/ የኤርትራን ብሔራዊ አንድነት ማጽደቅ: ለ/ በኢጣሊያን ተጠባባቂነት በተቻለ ፍጥነት ነጻነት ማስገኘት: ሐ/ በኤርትራውያንና በፈረንጆች መካከል የመብት እኩልነት እንዲኖር ማድረግ::

<u>5ኛ የምፅዋ የእስላሞች ብሔራዊ ቡድን</u>: የተመሠረተው በ1947: ያባሎች ቁጥር 56000: አባሎቹ በሙሉ እስላሞች ሲሆኑ ከነርሱ ውስጥ ሃያ አምስት ሺህ ደንከሎች ነበሩ::ፕሮግራሙ ሀ/ የኤርትራን ብሔራዊ አንድነት ማጽደቅ ለ/ በኢንተርናሽናላዊ ቁጥጥር ሥር በእንግሊዝ ተጠባባቂነት ላሥር ዓመት ከቆየ በኋላ ነጻነትን ማግኘት::

<u>6ኛ ያርበኞች ማህበር</u>: የፖሊቲካ ቡድን ባይሆን የሕዝብ ድርጅት የሆነ በዚያን ጊዜ የአባሎቹን መብትና ጥቅም ብቻ በመጠበቅ የተወሰነ ምንም ዓይነት የፖሊቲካ ፕሮግራም ያልነበረው ነበር::

የነዚህ ድርጅቶች ጠቅላላ አቋም ብንመለከት የኤርትራን ሕዝብ እውነተኛ ፍላጎትና ምኞት እስከምን ድረስ ሊወክሉት ወይም ሊገልጹት እንደቻሉ ለመገንዘብ ይቻላል::የመጀመርያው ማለት የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ቡድን ከድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በጥብቅ የተሣሠረ የባላባቶችና የመሳፍንት ቡድን እንደነበረ አይጠረጠርም::ሁለተኛው የእስላሞች ማህበር በባሎቹም በፕሮግራሙም የገበሩን ጥቅም ለመጠበቅ የተዘጋጀ በመጠኑ ሕዝባዊ ነበር ለማለት ይቻላል::ሶስተኛው ከባዕድ ካፒታል ጋር የተያያዘ የኮምፕራዶር ቡርዣ ቡድን,

አራተኛው በቀጥታ ለኢጣሊያን ኢምፔሪያሊስቶች የተሸጠ፡ አምስተኛው ገን
በመሠረቱ ሕዝባዊና የሠራተኞች ቡድን ሲሆን የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች በዘ
ዴ የያዙት ለመሆን ከፕሮግራሞቹ ለመገመት ይቻላል፡፡

ቀናው እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን ጉዳይ፡ ምንም እንኳን ድርጅቶ
ቹ ያበሉቻቸውን ቅር ከመጠን በላይ አብዝተው ቢበዙም፡ ምንም እንኳ በደ
ፈናው ያሳነሳቸ ማወላወል በገበሬውና በሠራተኛው ጥቅም ላይ የተመሠረተ ቡድ
ን ባይፀናርም፡ በእንግሊዞች አስተዳደር ሥር ሁኔታው አስከፊ ቀደ ደረሰ የኤር
ትራ ሕዝብ የምዕራባውያንን የቡርዧ ዲሞክራሲ ለጥቂት ዓመታት ለመቅመስ መቻ
ሉ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የሕዝቡ የፖሊቲካ ንቃት ከፍ ካለ ደረጃ ላይ ደ
ርሶ ስለነበር ከቀሩት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይለያል፡፡ ይህ በቀላሉ የሚታለፍ
ጉዳይ አይደለም፡፡—ለወደፊቱ ስለነዚህ ቡድኖችና ስለአቋቋማቸው ስለዚህ ዘመን
የኤርትራ ሕዝብ ታሪክና ከሙም ምን ትምህርት ሊገኝ እንደሚቻል ሰፊ ጥናት
ማድረግ ያስፈልጋል፡፡—

የሆነሆኖ ወደ ታሪኩ እንመለስና፡ ያራቱ መንግሥታት ኮሚሲዮን በዚህ
ሁኔታ ላይ ምንም ስምምነት ለማድረግ አልቻሉም፡፡ የኤርትራ ጉዳይ ወደ ተባበ
ሩት መንግሥታት እንዲተላለፍ ተደረገ፡፡ ይህ ሲሆን በ1941 በኒውዮርክ
ከተማ በሶስት ቡድኖችና ድርጅቶች ማለት የኤርትራ የእስላሞች ማህበር፡ ሊበ
ራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲ፡ ያዲሲቱ ኤርትራ ቡድን፡ የእስላሞች ብሔራዊ ቡድን፡
ያርበኞች ማህበርና የኤርትራና የኢጣሊያን ማህበር አንድነት ተሰማምተው
'የነጻነት ገንባር' ፈጠሩ፡፡ሁሉም በአንድነት ወዲያውኑ ኤርትራ ነጻነቷን እን
ድታገኝ ጠየቁ፡፡በ1950 ይህ ገንባር በውስጡ ሰባት የፖሊቲካ ቡድኖች ቢ
ይዝ ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ማለት የእስላሞች ማህበርና የኤርትራና የኢትዮጵያ
አንድነት ማህበር በቁጥርም በኃይልም ከሌሎች በልጠው የሚወዳደሩ ነበሩ፡፡

እላይ እንደተጠቀሰው የኤርትራ ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት ፊት ቢ
ቀርብ አዲስ ኮሚሲዮን —በርማ፡ ጉቴማላ፡ ኖርዌይ፡ ፓኪስታን፡ደቡብአፍሪካ



ያሉበት— ተፈጥሮ ሁኔታውን እንዲያጠና ወደ ኤርትራ ተላከ፡፡ቀጥሎም የግብ
ፅን የኢትዮጵያን የፈረንሳይንና የእንግሊዝን መንግሥታት አስተያየት ከሰማ
በኋላ ሕዝቡ ከሶስት ምርጫዎች አንዱን እንዲያደርግ ተወሰነ፡፡እነዚህም ምር
ጫዎች ወይ ከኢትዮጵያ ጋር መቀሐል ወይ ከኢትዮጵያ ጋር ፌዴራቢዮን ማድረግ
ያለዚያም ሳሥር ዓመት በተባበሩት መንግሥታት ተጠባባቂነት ሥር እንዲኖር መም
ረጥ ነበሩ፡፡

እንደሚያወስው ጉዳዩ በፌዴሬሽን ተወስና የተባበሩት መንግሥታት መል
እክተኛ ማቲዮንዞ ሕገመንግሥቱን ካዘጋጀ በኋላ በ1952 የሕዝብ ምርጫ ተደ
ርጎ 68 አባሎች ያሉበት ፓርላማ ተቋቋመ፡፡ በመስከረም 15 ቀን ተዱሳ በ
ይፋ የመንግሥቱን ሃላፊነት ቢወስዱ ወዲያውኑ የእንግሊዝ ወታደሮች በታቸውን
ለሁለት ሺህ የኢትዮጵያ ወታደሮች ለቀቁ፡፡

የኤርትራ ሕገመንግሥት አንቀጽ ስስት እንደሚገልጸው ሁሉ ኤርትራ ራ
ሱን የቻለ መንግሥት አቁሞ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዘውድ ሥር
ፌዴራቢዮን አደረገች፡፡የፌዴራቢዮኑ ሃላፊ መንግሥት ብሔራዊውን መከላከያ
የውጭ ጉዳይን የገንዘብንና የፊናንስን የንግዱንና የመገናኛን ሃላፊነት ሲወ
ስዱ ኤርትራ ግን የራስዋ የውስጥ አስተዳደር ነጻነት እንዲኖራት ተደረገ፡፡
እንቀጽ አራት 'የኤርትራ መንግሥቱ በሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ ማለት የሕግ
አወሳሰን፡ የሕግ አስፈጻሚነትና የፍርድ ሥልጣን አለው' ይላል፡፡ የፌዴራቡ
ዮኑንና የውስጣዊውን አስተዳደር የሥራ አከፋፈልና ሥልጣን ሕገመንግሥቱ በዝ
ርዝር በማያሻማ ደንብ ገልጾ ያሳያል፡፡

## 2 በባላባታዊው አገዛዝና በኤርትራ ሕዝብ መካከል ያሉት ቅራኔዎች

በሥሩ የፌዴራቢዮን ዓመታት ውስጥ የተደረጉትን ነገሮች ማገም ስለሚ
ያውቁ እዚህ ላይ በሰፊው መዘርዘር አያስፈልገም፡፡ አሁንሬው የኢትዮጵያ ነ

ሠ ነገሥት መንግሥት በተለመዱት መሣርያዎች በመጠቀም፡ እስላሙንና ክርስቲያ
ኑን፡ ደገኛውንና ቆለኛውን፡ የኤርትራን ነዋሪዎች እርስበርስ በማጋጨት፡ አገ·
ልጋዮች ሃብትን በመሸም፡ ርስት በመስጠት፡ ሹማምንትን በገንዘብ በመግዛት፡
በማታለል፡ በማስፈራራት፡ የኤርትራን ሕገመንግሥት እንደረሱ ሕገመንግሥት የ
ብጫሽ ወረቀት ጉዳይ ብቻ በማድረግ፡ በለመደው ተንኮሉ ሁሉ በመጠቀም፡ የበ
ሳበቶ አገዛዝ ዲክቴተርሺፕን አስፈረበት፡፡ ቀድሞ የነበሩት የቡርዢ ብዴኖች
ጋዜጦችም ጠፉ፡፡ለቀረት ዓመታት ያህል የቡርዢ ዴሞክራሲ ቀምሶ የነበረው የኤ
ርትራ ሕዝብ ወደኋላ ተመልሶ በባላባታዊ አገዛዝ ሥር እንዲወድቅ ተደረገ፡፡

አድሃሪው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከላይ የተዘረዘሩትን
የፖሊቲካና የኢኮኖሚክ ጭቆናዎች ብቻ ሳይሆን የባሕልም፡ የሕብረተሰባዊንም ጭ
ቆና በሕዝቡ ላይ አስፈረበት፡፡ ከዚህ አልፎ ተርፎ ደግሞ የኤርትራን ምድር
የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች የጦር ማረፊያ እንዲያደርጊት አሳልፎ ሸጠት፡፡
ለትንሽ ጊዜ የቡርዢን ዴሞክራሲ ቀምሶ የነበረው የኤርትራ ሕዝብ በዚህ አኳ
ኋን ወደኋላ ከተመለሰ በኋላ እንደሚታወሰው በ1962 ወደኋላ ለመመለሱ ሕጋዊ
ማስረጃ ይኖር ዘንድ አድሃሪው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥ ኤርትራን
ጠቅላይ ግዛት አድርጊት አረፈ፡፡

ዛሬ በኤርትራ ሕዝብ ላይ የሠፈረው የጭቆና አገዛዝ በሌሎቹ የኢት
ዮጵያ ሕዝቦች ላይ ከሠፈረው የጭቆና አገዛዝ በምንም አይለይም፡፡ባድሃሪው
ባላባታዊ አገዛዝና በኤርትራ ሕዝብ መካከል ያሉት ቅራኔዎች ከሥረመሠረታቸው
በቀሩት የኢትዮጵያ ሕዝቦችና በገዛዙ መካከል ካሉት ቅራኔዎች አይለዩም፡፡
እንደዚሁም በኤርትራ ሕዝብ በራሱ ዉስጥ ያሉት የሁለተኛ ደረጃ ሕብረተሰባዊ ቅ
ራኔዎች ማለት የነገድ፡ የሃይማኖት፡ የባሕል የቋንቋ፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውስ
ጥ የሚገኙ ቅራኔዎች ናቸው፡፡

አድሃሪው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የኤርትራን ሕዝብ ለመ



ጨቆን የሚጠቀምበትን መሣርያ፡ ቦምቡ፡ ናፓልሙ፡ የወታደር ትጥቁ ከአሜሪካን
ኢምፔሪያሊስቶች የተሰጡ ናቸው፡፡ የኤርትራን ምድር የተፈጥሮ ሃብትና የሠራ
ተኛውን የገበሬውን የሥራፍሬ ድካምና ላብ የሚጠቀሙበት በቀጥታም ሆነ በተዘዋ
ዋሪ መንገድ ኢምፔሪያሊስቶችና ገብረ አበሮቻቸው ናቸው፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ዛሬ የኢትዮጵያም ሕዝቦች የኤርትራም ሕዝብ ዋ
ና ጠላቶች ባላባታዊው አገዛዝና የበላዩ ተጠባባቂው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም
መሆናቸው ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልጽ መሆን አለበቸው፡፡በባላባቱና በገበሬው
መካከል፡ በካፒታሊስቶችና በሠራተኛው መካከል፡ባገሬቱ ሕዝቦችና በኢምፔሪያሊ
ስቶች መካከል ያሉት ቅራኔዎች ተጻራሪ —አንታጎኒስቲክ— የመጀመርያ ደረጃ
ከሁሉ አስቀድሞ መፈታት ያለባቸው ቅራኔዎች ናቸው፡፡እነዚህንም የሚፈታቸው
ማለት የኢትዮጵያንና የኤርትራን ሕዝቦች ከጭቆና ሊያወጣቸውና አዲስ ሕብረተሰብ
ሊያሥራቸው የሚችል ትክክለኛ ሬቮሊሲዮናዊ አመራር ያለው ሕዝባዊ ጦርነት ብቻ
ነው፡፡ይህን መሠረታዊ ጉዳይ ከተረዳን ወዲያ እስቲ ደግሞ ወደ 'ግንባሩ'
ፖሊቲካ ተመልሰን እስከምን ድረስ ሕዝባዊ አመራር እንዳለው እንይ፡፡

## 3 የኤርትራ ነጻነት ግንባር መሪዎችና ፖሊቲካቸው

እኔ እስከማውቀው ድረስ በዛሬው ግንባር መሪዎች ብዙዎቹ ቀንት አሳያ
ከተጠቀሱት ቡድኖችና ድርጅቶች ውስጥ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ቀደም ብለን እን
ዳየነው ሁሉ ከቀንቶቹ ቡድኖችና ድርጅቶች ውስጥ ያሰቀርጨሩ የገበሬውንና የሠ
ራተኛውን ወገን የሚወክል አንዱም አልነበረም፡፡አንዳንዶቹ ከአድሃሪው የኢት
ዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትጋር፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ወይ ከእንግሊዝ ወይ ከ
ኢጣሊያን ኢምፔሪያሊስቶች ጋር የተባበሩ፡ የቀሩት ደግሞ ምንም ዓይነት የተ
ጣራ የፖሊቲካ መሥመር የሌላቸው ነበሩ፡፡በመሠረቱ ሕዝባዊና ሬቮሉሽናዊ የሆነ
ቡድን አልነበረም፡፡ዛሬም በግንባሩ አመራርላይ የሚገኙት ብዙዎቹ ከኮምፕራደር

ማለት ዘውዱ ካፒታል ተገኘነት ሥር የሚኖሩ ከቡርዧ መደብ የወጡ ናቸው::
የኤርትራን ሕዝብ ከበሳባታዊ አገዛዝና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ከሚያደርገው
ትግል ትክክለኛ አመራር በጥ ተውት ወደድል ሲመሩት እንደማይችሉ የታወቀ ነው::

ገንባሩ እስካሁን ድረስ እንዲም የተብራ ፕሮግራም ያወጣ አይመስለኝ
ም:: ቢያወጣም አሳየሁም: ምንም ያህል አሳበራዘውም ማለት ነው::ነገር ገን
በየጊዜው ከሚበትኗቸው ጽሑፎች ለምሳሌ:- ሜምራንደም ቶ ኪ ኬስ ፎ ኢ፤
ኤሪትሪያን ሊበሬሽን ፍሮንት ኢን ፎሬን ፕረስ ከሚባሉት የእንግሊዝኛ ጽሑፍ
ች የሚቀጥሉት ናቸው:: 1ኛ የገንባሩ ግብ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ነጥሎ ለብቻ
ነጻ አገር ማድረግ ነው:: 2ኛ ለዚህም ግብ ዋና መሣርያ ብሎ የሚያምነው
የኤርትራ ጉዳይ ወደተባበሩት መንግሥታት መቅረብ ቢሆን ለጊዜው የሚያደርገው
ጦርነት ወደዚህ ወደተባለው ድርጅት በፍጥነት እንዲመራው ነው::እንደተፈለገው
እንዲያውም ቢቻል ኖሮና ኤርትራ ነጻ ብትወጣ ከቀረው ኢትዮጵያ ጋር ምን ዓይ
ነት ግንኙነት ይኖራታል? የኤርትራስ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፡ ፖሊቲካዊና ሕብረሰ
ባዊ አኗም ምን ዓይነት ለውጥ ይደርስበታል? ነጻ የወጣች ኤርትራ ኢምፔሪያ
ሊዝምን ምን ልታደርገው ነው? ለነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች እስካሁን ድረስ
ከገንባሩ ምንም መልስ አልተሰጠም::

አሳይ ከተጠቀሱት መጽሔትና ጽሑፎች በመጀመርያው ውስጥ የኤርትራ የ
ነጻነት ገንባር በኢጣርጃ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ወደኢትዮጵያ
ተመልበ ሲሳ የነጻነት ገንባር እንዲከፍት ያስስበዋል::በሁለተኛው ውስጥ ደ
ግሞ እንዴ በጣም የሚያስገርም ወሬ አለ::እንዴ ሰዎን የገንባሩ ሰዎች በኤ
ርትሬ ሁለት ፈረንጆችን ያዙዋቸው::እነዚህ ፈረንጆች ከተመረመሩ በኋላ አሜ
ሪካኖች መሆናቸው ሲታወቅ'እስራኤላውያን መሰላችሁን ነው እንጂ አሜሪካንማ
አንነካም' ብለው ተለቀቁ:: የተማሪን ድርጅት ገንባር አቃሎ ብሎ መጋበዝና
ምናልባት ለበሳባታዊው መንግሥት ሆን ሳሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ለሳይ የሆ
ትትን ሰዎች ለነጻ መልቀቅ ምን ያህል የፖሊቲካ ደካማነት እንዳለ የሚያስበ



ነገር ነው::

የገንባሩ ሰዎች የሚደገፉት በዐረብ አገሮች ነው ይባላል፡ ነገር ገን
ልክ እንደተቀበዮቻቸው እንደአረብ እንደ ዐረብ አገሮች ሁሉ እስራኤል ያሜሪ
ካን ኢምፔሪያሊዝም ቀኝ እጅና ታዛዥ በመሆኗ ዋናው የአረብ ሕዝቦች ጠላት
በዋናይትድ ስቴትስ የሚመራው ኢምፔሪያሊዝም መሆኑን የተገነዘቡት አይመስለኝ
ም:: እንዲያውም እንደሚወራው ከሆነ ትልልቅ የገንባሩ መሪዎች ካሜሪካን ኢ
ምፔሪያሊስቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው ይባላል::የዚህ ዓይነቱ ፖሊቲ
ካው መሳቅቅ የሌለው ገንባር እንዴት አድርጎ የኤርትራ ሕዝብ ድልን እንዲቀ
ዳጅ ሊመራው ይችላል?

## 4 የገንባሩ የወደፊት ዕድልና የኤርትራ ሕዝብ ተጋድሎ

'የኤርትራ የነጻነት ገንባር' መቶበመቶ ከሽፍትነት ብሎ መገመት ከስ
ህተት ይቆጥራል::በገንባሩ ውስጥ ለወደፊት [redacted] ብዙ የፖሊቲካ ትግል እን
ደሚኖርና ገንባሩ ብዙ ፈተና እንደሚደርስበት አይጠረጠርም:: እነዚህ 'ታሳቂ
የፖሊቲካ ሰዎች' የተባሉት የቡርዧ መሪዎች በእንግሊዞች ሥር የለመዱትን የ
ቡርዧ ዲሞክራሲ በነገዲህ አያገኙትምና የገዙ ያሕዝብ ቀቅምን መሠረት አድር
ገው ከሚነሡ ቀን ረፓብሊካኖች ወንበሳቸው አይቀርም::እነዚህ እውነተኛ
ረፓብሊካኖች በገንባሩም ውስጥ በኤርትራም ሕዝብ ውስጥ መገኘታቸው ስለማ
ይቀር በዚህ በኩል ገንባሩ አንዳች ጥቅም ስጥቷል ለማለት ይቻላል::

የኤርትራ ሕዝብ ተጋድሎ ገን ትክክለኛ ተጋድሎ ነው::የኤርትራ ሕዝ
ብ ተጋድሎ ዘተፋት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተጋድሎ የማይነጠል የማይገመስ እንዴ
አካል ስለሆነ የኤርትራ ነጻነት በኢትዮጵያ ነጻነት ያልፋል::በመሠረታቸው
የኤርትራ ሕዝብ፡ የብረና ሕዝብ፡ የባሌ ሕዝብ የያዙዋቸው ትግሎች ትክክለኛ
በመሆናቸው በመጠረቭ ባሳባታዊው አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝምን ያሸንፉሉ::

በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ ዘሬ የሚንፀሰው ረፐብሊካዊ ሕዝባዊ አ
መራር ብቻ ነው::በገዛዙና በሕዝቦች መካከል፡ በኢምፔሪያሊዝምና በአገሬቷ
መካከል ያሉትን ተጻጻሪ ቅራኔዎች፡ በሕዝቡ ውስጥ ያሉትን የሁለተኛ ደረጃ
ቅራኔዎች በየዘርፍ በየዘርፉ መርምሮ ያወቀ፡ ከሠራተኛውን ከገበሬው ጋር በ
መዋሃዱ በይገባዊ የሕዝብ ጦርነት ለመምራት የሚችል፡ በሠራፋ ዘዴና በምር
መራው፡ በዓለም አስተያየቱ ረፐብሊካዊ የሆነ ድርጅት ያስፈልገናል::የኤር
ትራ ሕዝብ ትግል ትክክለኛ ሆኖ ባለ የገንበሩ የፖሊቲካ አመራር ገን ሕዝብ
ዊ አይደሰም ያልሆት ይህን ሁሉ በመሠልከት ነው::



## ቤቱ አንዳይፈርስ አድኃሪ አንዳይነግሥ

ከናይዝጊ ክፍሉ

ማንኛውም ዓይነት ታሪካዊ ለውጥ የተወበጠ አቢጋንና ሁኔታ ደረጃና
ልዩ ምክንያት የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን የአንድ ሕብረሰብ ለውጥም ይህን
ዓይነት ምርመራ የሚጠይቅ ነው::በአውሮፓ የሚገኘው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህ
በር በምን ዓይነት ጎዳና እንደተጓዘ ልብ ብሎ ለመጀመርያ ለተመለከተው ሰው
ለማወቅ የሚያስቸግር አይደለም::ይህ ማህበር በኢትዮጵያና በሰሜን አሜሪካ አ
ንደሚገኙት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበሮች የሚጠይቁትና የሚያሰማው አቤቱታ:—

1ኛ ከአፍሪካ ገንበር ከደምት የነበረችው አገራችን ወደኋላ ቀርታ
ለች፡ 2ኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ በድህነት በሽታ ተጎድቷል፡ 3ኛ የሀገሬቱ ሀብት
በጥቂት ሃብታሞችና በውጭ አገር ሰዎች ይዘረፋል የሚል ነው::አክብታችን የተ
ቀበረበት አገራችን፡ ጦሙን አየዋለ አያደረ የሚያስተምረን ሕዝባችንን አገርዓ፡
ጠበቃእንሁንላቸው፡ ዓይናቸው ታውርአልና መድኃኒት አገፈልገላቸው አያ መሬት
ሳራቡ ይሰጠው ቢል፡ ለሕዝቡ መብት በመጠየቅ ብዙ ዘቻዎችንና አንቀፋቶችን
ያለፈ ነው::

አያገዓገዱ ፊደል የቀጠረ ኢትዮጵያዊ የትም ቦታ በኖር እነዚህ ነገሮ
ች ፍጻሜ እንዲያገኙ ትፈልጋለህን? ብሎ ቢጠየቅ እሉታ መልስ የሚገኝ አይመ
ስለኝም::እንዲያውም በበለጠ ቢቆጭና የንዴት መንፈስ በየቦታው ቢያሰማ ይታ
ያል::መሆሬን የሚበሉት ኢትዮጵያውያን አስተባሰበና ዘዴ በሁለት ተቃራኒ መን
ገዱ የሚሬመዱ ነው:: ይኸውም ሀ የወደኛና ለ የተወደኛ ወገን ብዬ ልደለዱላ
ቸው አፈቀዓለሁ::የወደኛ ወገን ደጋፊ መሆሬን በገዱ በኩል የሕዝቡንና የሀገ
ሬቱን ደህንነት ፈላጊ መስለው አታላይ ፖሊቲካ እየተከተሉ በሌላ በኩል ደኅም
የፍርሃትና የገል ቀቅም መንፈስ አባድረው በገንዘብና በጊዜያዊ ሃብት እየተታ

ለሉና እየተደለሉ የኢኮኖታቸው ተፃራኒ ባርያ የሚሆኑ ናቸው::እነዚህ ቡርዧም ለመሆን የሚመኙ ምሁራን የጽሑፍ የንግግርና የሃሳብ ነጻነት ለማግኘት ብቻ የሚጥሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ባለበት ሁኔታ እንዲኖርና አቤት ጌታዬ እያለ እንደጣሉት እንዲያመልካቸው የሚመኙ: መሠረታዊ ለውጥ እንዳይደረግ የሚሹ ቢኖሩም መላአከት ከሰማይ ወርደው የሚያደርጉትን ለውጥ ለማየት የሚጠባበቁ ወይም ደግም ሌላ ሰው በሠራው ቤት ለመኖር እንቁ ያዘጋጀውን ምግብ ለመብላት የሚጓጉ: መሬታቸውን ሳያርሱ እህል የሚያበቅሉ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ቴዎዶሮቦች ነን የሚሉ ናቸው::በኤውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በእንግሊዝ አገር በኬንት ባደረገው ስድስተኛ ጉባኤ 'ከገዥ ቤተሰብ መወለድ ብቻ እረቡ በጠቀሳለው በኢትዮጵያ የሰቨልና የፖሊቲካ ልምድ መሠረት ልዩ ሥፍራ የሚሰጥ እረቡን የቻለ ምንጭ ነው::የንጉሥ ነገሥቱም ቤተ ሰብ በመሠረቱ የነዚሁ የገዥ ቤተ ሰቦች ፖሊቲካ ትግል ቀጥተኛ ውጤት በመሆኑ እነዚ ቤተ ሰቦች ያላቸውን ጠቀሳሳ ሚዛን በመጠበቅ በስተቀር ወርስ እንዳያጠሩቸው የረቡ አቋም ያስገድደቀል::እነዚህም የባላባት ቤተሰቦች በየጊዜው የሚያስቁት የፖሊቲካና የገዢ ስልፌኛነት —ለከፍተኛ የፖሊቲካ ኃይል በማሸማት በስተቀር— የተበላሸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ፖሊቲካና ኢኮኖሚክ ሁኔታ በመሠረቱ እንዳይሠሩ የራሳቸው የቤተ ሰብ አቋም ያስገድዳቸዋል:: ብሉ የሰጠውን ውሳኔ እያስታወሰን አቤቱ ጌታዬ በወዳጆቼ ጠብቀኝ እንጂ ከጠላቶቼስ ራሴን እጠብቃለሁ እንደሚባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጀመርያ ችግርም እነዚህ በአፍ የሱ ጠባቂች መስለው ሐባባቸው ግን ግላዊ ኑሮአቸውን ለማደላደል የሚያስሳስሉ አገዶ እንገሬቸው ገደል አፋፍ ላይ ተንጠልጥሎ ሌላው ደግሞ በኢምፔሪያሉ በት አዘቀት ውስጥ የተነከረ የበግ ለምዱ የለበሱ ተኩሎች የኢትዮጵያ ሕዝብን የሚያንገላቱና የሚያበዘብዙ ወይም ደግሞ የዚህ ዓይነት ሕልም ያላቸው የሕዝብ ጠላት የሆኑ ምሁራን የነገ ባላበቶች ለመሆን በተበሩ የሚጠባበቁ የሚፈጥሩት ተንኮል ነው::



እነዚህ ገማሽ አካላቸው የበሰበሰ ገማሹ ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የተበከለ ያገር ነቀርሳዎች እንዳጋጣሚ ሆኖ በተቀደሰው የኢትዮጵያ ምድር እንደጉንዳን ስለፈሉ ነው እንጂ በእውነቱስ ደቂቅም ተገዢዎች ጉዳይ በታጠቀ አምዱ ላይ ቦታ ማግኘት አይገባቸውም ነበር::

ኢትዮጵያ በብዙ ብሔሮች ቋንቋዎችና ባሕሎች የሆነች በእድገት ላይ የምትገኝ አገር ስትሆን ለእድገቷም ሆነ ወጣት ትውልዱ የሚመኝላትን ብልጽግና እገቡ ለማድረስ የሚቻለው እነዚህ ብሔሮችና ነገዶች በሕብረት በአንድነትና በትጋት ሲሠሩ ነው::ይህ የጎረቤት አገሮችና የክፍለ ዓለሞች ግስጋሴ አያስቀናው የሚያየውንና የሚሰማውን ጥሩ ነገር ሁሉ ለሀገሩና ለሕዝቡ የሚመኝ የከሰመነውና የተጨቆነው የመንፈስ ጽኑ ኢትዮጵያዊ ወገንና ጠበቃ የሚከተለው ሐሳብ ሲሆን: የአርኩስ ዘሮችና የኢትዮጵያ ነቀርሶች ግን ይዞታቸው እንዳይቀነስ በመፍራት እኔ ብቻ ልኑር በሚል ሐሳብ በመመራት እንዲሁም ያበቃቻቸውን እርአያ በመከተል የኢትዮጵያ ሕዝብን አንድነት ለማሰናከል የዘር የባሕልና የቋንቋ ልዩነት ጠንቅ እየተበቀሉ ሕዝቡን አበጫብጭው ከፋፍለው ለመግዛት ይጥራሉ:: በኤውሮፓ የሚገኘው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ባለፉት ሰባት ዓመታት በተለይም ከታሪካዊው የ፲፬ና ጉባኤ ጀምሮ እንኳንስ ያንድ ሕዝብ አንድነትና የክፍለ ዓለም ሕዝቦች ሕብረት እንኳን ለእድገት ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ በባለፉቸው ውሳኔዎች የዚህ ዓይነት ተንኮል ማወገዙንና መቃወሙን መረሳት የለበትም::

ስለዚህ በኤውሮፓ የሚገኘው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የአድኃሪው ወገን ተቃዋሚ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠበቃ መሆኑ ከተረጋገጠ ማንኛውም ማንኛውም ስለኤውሮፓ ማህበር አቋምና ዓላማ የውሸት ፕሮፓጋንዳ የሚያስወሩ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እውነተኛውን ነገር እንዳይገነዘብ ለማድረግ የሚሞከረውን የግል እንጀራውን ለማውጣት የሚከጅለውን ሁሉ የሃገር ነቀርሳዎች

በልጋቸው ጥፍረች ውስጥ የሚኖር ስለሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑን
ይወቀው::

እዚህ ላይ አንባቢ እንዲገነዘብልኝ የምፈልገው የኢትዮጵያ ተማሪዎ
ች ማህበር በኢውሮፓ ፍጹም ነው ስህተት የለበትም ማለቴ አይደለም::አፃን
የጐለበት ባይሆን የሃብት እጥረት አለበት: በይበልጥ ደግሞ የሥርዐቱ አቋም
ሙሉ ሥልጣን ያልጠበጠ የወቷኝና የዘወቷኝ ተቃራኒዎች ያለበት ሸንጎ በመሆኑ
የሚጠበቀው የኢኮኖሚክስና የሕብረተሰብ መሠረታዊ ለውጥ ብዙ እንቅፋቶች ቢያጋጥ
ሙት እናያለን:: በእውነቱ የምንታርዜው ውሳኔኦችንበሥራ ላይ እንዲውል ከተ
ፈለገ የኢውሮፓው ማህበራችን ማለት ለዘወቀነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠበቃ መሆ
ናችንን የምናረጋግጥ ከሆነ የተወቃ አህል ሆነን ማህበራችንን እያጠነከርን
የሕዝቦችንን መብት እንጠይቅ: እኔ ከሞትሁ በኋላ ሰርዶ አይብቀል እንዳንሆነ
ገን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በኢውሮፓ ሌላ መስመርና አስትራቴጂ መውስ
ዱ የሚያስፈልገው አሁን ነው::

የአህልና የአረም ቅልቅል በዝቶ አገሪቷና ሕዝቡ ከሚረቡ የአባልነ
ት ልዩ ሕግና ነዓጁ ተወስኖ ሐብቡን አገቡ ያሥርስ:: የኋላኋላ ብልሁ የኢ
ትዮጵያ ሕዝብ ደጋፊውና ነቂው ማን መሆኑን ስይገነዘበው ስለማይቀር የኢውሮ
ፓ ማህበራችን የተማሪ አባል አንስተኛነት ሊያስስበው የሚገባ አይደለም::
ዋናው ነገር ደግሞ የሐሳቡና የመንፈስ አንዱነት ነው የሚፈለገው እንጂበኢ
ውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ሐሳብ የሚደገፍ አባል በምሳው የዘጠ
ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን እናስታውስ::

እያንዳንዱ በኢውሮፓ የሚገኘው የሕዝብ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊ በኢው
ሮፓ አንዱ ማህበር ብቻ መኖሩን ይህን ማህበር የሚቃወሙም የአሁሃሪዎች ክፍ
ልና ሕዝቦችንን ለመዉቀን የተነሣ መሆኑን እንዲያውቀው ያስፈልጋል::



## በኢምፔሪያሊዝምና በሶስተኛው ዓለም መካከል ያለው የፕሮዳክሽን ግንኙነት

የጻፈው:- ፒ ዞላ [1]
የተረጐመው:- ስዒም ገንዔ

ባለፈው ምዕራፍ በካፒታሳዊ አገዛዝ ስር ከሚኖሩት አገሮች ውስጥ
በሀ- ገውስ ክፍል የተመደቡትን ወደፊት የተራመዱ ካፒታሳዊ አገሮች 'ኢም
ፔሪያሳዊ አገሮች' ወይም በጭሩ 'ኢምፔሪያሊዝም' ብለን እንጠራቸዋለን:: በያ
ሜው አጭር ከመሆኑ በላይ ከእውነተኛው ሁኔታ ጋር ይስማማል:: በትክክለኛው
መንገዱ የኢምፔሪያሊዝም ትርጉም የቀኘ ገዛቶች በሉቀቸው ወይም በኢኮኖሚና
በፖሊቲካ ተገኖች በሆኑት አገሮች ላይ ሥልጣናቸውን በዘረጉት [redacted] አገ
ሮች —ለምሳሌ የአሜሪካን መንግሥት በላቲን አሜሪካ ላይ— ብቻ ሊወሰን
አይችልም:: ኢምፔሪያሊዝም የበለጠውን ኢኮኖሚ ነክ ነው::በዓለም የሥራ ክፍ
ያ፤: የልውውጦችን: የካፒታሎችን መዘዋወር ይወምራል:: እንደስዊድንና እንደ
ስዊቶዘርላንዱ ያሉ አገሮች ምንም ዓይነት ቀኘ ገዛት ያልነበራቸው: እንዲም
ወደኋላ በቀረ አገር ላይ ሥልጣናቸውን ያልዘረጉ: በዓይነት ረገዱ ከአሜሪካ
ወይም ከታላቷ ብርታኒያ ያነሱ ኢምፔሪያሳዊ አይደሉም:: በብዛት ረገዱ ብቻ
አነስ ባለ አቧኋን ናቸው:: ይኸውም ቢሆን ዛሬ ቀናፖሳዊ ወይም ኦሊጎፖሳዊ
ካፒታል የበለጠውን ዓለምአቀፍ እያሆኑንበሚኬዴበት ወቅት ለመስፈር ወይም ለመ
ለካት አስቸጋሪ ነው::

ኢምፔሪያሳዊ አገሮችና የሶስተኛው ዓለም አገሮች በዋናቶ በዓለም
ፕሮዳክሽኖች —ውጤተ ሥራዎች— ውስጥ ምን ያህል እንደሚሳተፉ ማስየትና

---

1 'ለ ፒሳዠ ዱ ቲየር ሞንዴ' ከፒየር ዞላ:: የሁለተኛው ምዕራፍ 'ፊፖር
እንትር ለምፔሪያሊዝም ኤ ለ ቲየር ሞንዴ ዓን ለ ደሜን ደ ላ ፕሮዱ
ክሲዮን':: የተረጐመው የብርዕ ስሙ ስዒም ገንዔ የሚባል በኢውሮፓ የሚ
ገኘ አንዱ ኢትዮጵያዊ ተማሪ ነው::

ከዚህ ውስጥ የሚፈልቀውን ተገናኝ ግንኙነት ወይም ዝምድና ማግኘት ይህ ነው የዚህ ምዕራፍ ግብ፡፡ ፕሮዳክሽን ነክ የሆኑትን አስረጃዎች መመርመር ምንም እንኳ ጠቃሚ ነገሮች ቢያስገኝም በሙሉ የምንጠባበቀውን ሊሰጥ የሚችለው ከሌሎች አስረጂዎች ጥናት በተለይ ከልውውጦች —ምዕራፍ 3— ውጤቶች ጋር ሲጋጠምና ቢያያዝ መሆኑን ከአሁኑ ማመልከት ያስፈልጋል፡፡

<u>ሀ— የማዕድን ኢንዱስትሪዎች፡—</u> የምድር ውስጥን ሃብት በማውጣት የሶስተኛውን ዓለምና የኢምፔሪያሳዊ አገሮችን ድርሻዎች ትልቅነት ጠቅላላ መለኪያ ለማግኘት የቻልነው በ1958 የማዕድን ኢንዱስትሪዎች የተጣማሪ ዋጋ መቷዊ ማከፋፈያ ከሰንጠረዥ 11 ከተባበሩት መንግሥታት የ1962 ዓመታዊ አስታቲስቲክስ ብቻ ነው፡፡ ይህውም የሚቀጥለውን ሰንጠረዥ ለማዘጋጀት አስችሎናል፡፡

| የዓለም ክፍሎች | የማዕድን ኢንዱስ ሁሉ | ዋናዎቹ ክፍሎች — ከሰል % | ሜታል % | ቤንዚን ጋዝ % |
|---|---|---|---|---|
| አፍሪቃና መካከለኛ ምሥራቅ | 13.5 % | 1.1 | 26.9 | 17.1 |
| ላቲን አሜሪካ | 8.4 | 0.6 | 13.3 | 12.4 |
| እስያ፡ከጃፓንና ከሶሻሊስት አገር ሌላ | 4.7 | 2.7 | 5.0 | 6.4 |
| ድምር | 26.6 | 4.4 | 45.2 | 35.9 |
| አሜሪካና ካናዳ | 44.6 | 20.7 | 34.5 | 61.3 |
| አውሮፓ ከሶሻሊስት አገሮች ሌላ | 25.5 | 67.1 | 15.2 | 2.7 |
| ጃፓን | 2.2 | 6.3 | 2.6 | 00.1 |
| ኦሺያኒያ | 1.1 | 1.5 | 2.5 | — |
| ድምር | 73.4 | 95.6 | 54.8 | 64.1 |
| የዓለም ጠቅላላ ድምር፡ከሶሻሊስት አገሮች በስተቀር | 100 | 100 | 100 | 100 |

በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ የሚታዩት አገሮች ለትንሽ የሶስተኛውን ዓለም አገሮችና ወደፊት የተራመዱትን ካፒታሳዊ አገሮች ከዚህ ቀደም ብሎ የተገለ



ጹትን ይመስላሉ፡፡ከእነዚህ አስረጂዎች እንደሚታየው በጠቅላላው በማዕድን ኢንዱስትሪ ረገድ የሶስተኛው ዓለም ፕሮዳክሽን አስተዋፅዖ ገና በ1958 ከኢምፔሪያሳዊ አገሮች ብሶ በልጦ ነበር፡፡ ይህ ፕሮዳክሽን በከሰል በኩል በጣም አነስተኛም ቢሆንም በቤንዚን በተለይም በሜታል በኩል በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡

ሆኖም ይህ በ1958 ነበር፡፡በተባበሩት መንግሥታት በ1964 ዓመታዊ አስታቲስቲክ መሠረት የማዕድን ኢንዱስትሪዎች የፕሮዳክሽን ኢንዴክሶች —የ1958 እንደ 100 የተወሰደ እንደሆነ— በኢንዱስትሪ የተራመዱት አገሮች ከ77 በ1948 ወደ 115 በ1964 —9 ወር— (+38)፡ በዚሁ ጊዜ ውስጥ የተባበሩት መንግሥታት 'በኢንዱስትሪ ያደጉ' የሚሏቸው አገሮች ከ45 ወደ 183 አልፈዋል፡፡ እነዚህ ቁጥሮች የሶስተኛውን ዓለም በዚህ ረገድ በኃይል ወደላይ መውጣት ይመሰክራሉ፡፡ ከ1958 እስከ 1964 የሶስተኛው ዓለም ፕሮዳክሽን በ83 በመቶ ሲያድግ የኢምፔሪያሳዊ አገሮች በ15 በመቶ ብቻ ከፍ አሉ፡፡ እንግዲህ በ1964 በጠቅላላው የማዕድን ኢንዱስትሪዎች ሶሻሊስት ባልሆነው ዓለም ውስጥ የሶስተኛው ዓለም ድርሻ 36.5 በመቶ የኢምፔሪያሳዊ አገሮች ድርሻ 63.5 ናቸው ብሎ ለመገመት ይቻላል፡፡ በስድስት ዓመታት ውስጥ የያገ ዓገቱ ማዕድን ቦታ እንደተለዋወጠ ለማየት ይቻላል፡ የበለጠ ለውጥ የተደረገው በሜታልና በቤንዚን በኩል ነው፡፡

ጥሬ ቤንዚን በሚመለከተው ረገድ የተባበሩት መንግሥታት አስታቲስቲክ እንደሚያስረዳው ከ1300 ሚሊዎን ቶን በዓለም ውስጥ ከ650 ሚሊዎን ቶን ጥቂት ፈሪ በማውጣት የሶስተኛው ዓለም አገሮች ከ425 ሚሊዎን ቶን —አሜሪካ ብቻ 372 ሚሊዎን ቶን — የበለጠ ያሳወጡትን ኢምፔሪያሳዊ አገሮች ገና ድሮ በጣም በልጠዋቸው ነበር፡፡

የሶስተኛው ዓለም ቦታ በብረት ማዕድን በኩል ገና ደካማ ቢሆንም —20 በመቶ ያህል ከዓለም— ብረት ባልሆኑት ሜታሎች በጣም ጠንካራ ነው፡፡ በሚከተሉት ቁጥሮች ለመገመት ይቻላል፡፡

በ1963 ከወጣው ከዓለም —ሶቭየትሕብረትና ቻይና ጭምር— 4050000 ቶን መዳብ ውስጥ የሦስተኛው ዓለም አገሮች ድርሻ 2 ሚሊዮን ቶን ማለት ከጠቅላላው ግማሽ ያህል ነው:: በማንጋኒዝ ይበልጡ ቦታቸው የተሻለ ነው:: በ1962 ከዓለም —ከቻይና በስተቀር— 5900000 ቶን ሶቭየትሕብረትን —2900000— የቀነስን እንደሆነ ከሦስት ሚሊዮን ቶን 2650000 ቶን አውጥተዋል:: እንደዚሁም በክብደት በኩል ቦታቸው ከፍ ያለ ነው:: ሦስት የአፍሪካ አገሮች ማለት ኮንጎ ኪንሻሳ: የቀድሞው የሮዴዢያና የኒያባሳንድ ፌዴሬሽን: ሞሮኮ: የሶቭየትሕብረትን ሳንቆጥር: በዓለም የወጣው ጠቅላላ 16700 ቶን 12000 ቶን አውጥተዋል:: በክሮም በኩል ቦታቸውም ደህና ነው:: በ1962 ከሶሻሊስት አገሮች በስተቀር በዓለም 1260000 ቶን ፕሮዳክሽን ውስጥ 930000 ቶን —ከዚሁም 400000 ከደቡብ አፍሪካ ብቻ— ከሦስተኛው ዓለም ነው የተገኘ:: በ1961 ከሶቭየት ሕብረት በስተቀር ከዓለም 165000 ቶን ከሦስተኛው ዓለም የተገኘ ነው:: ከ25ሚሊዮን ቦክሲት ቶን የዓለም ፕሮዳክሽን —የሶቭየት ሕብረትና ቻይና ሳይቆጠሩ— 17 ሚሊዮን ቶን ከሦስተኛው ዓለም የወጣ ነው:: የአንቲሞኒን ፕሮዳክሽን ያስገርማል:: በ1961 የዓለም 56200 ቶን በመላ ከሶሻሊስት አገሮችና —28350— ከሦስተኛው ዓለም —23180— የወጣ ነው::

በ1962 ሶሻሊስት ካልሆነው ዓለም የዚንክ አርቦው: የአረር ሲሶው: የወጣው ከሦስተኛው ዓለም ነው:: ብረት ያልሆኑት ሜታሎችን ዝርዝር ከመወረባችን በፊት ደቡብ አፍሪቃ የዓለምን ሰባት አስረኛ ወርቅ የምታወጣ መሆኗን እናስታውሳለን::

በዚሁ በምድር ውስጥ ሀብት ረገድ በ1961 ሦስት የአፍሪካ አገሮች በአንድነት 70 በመቶ ከዓለም አልማዝ —ኮንጎ ኪንሻሳ 50 በመቶ: ደቡብ አፍሪካና ጋና እያንዳንዳቸው 10 በመቶ— አውጥተዋል:: በ1962 ሶሻሊስት ያልሆነው ዓለም የዱኘ ፕሮዳክሽን 37 ሚሊዮን ቶን በመላ በአሜ



ካና —19700000 ቶን— በሦስተኛው —16630000 ቶን ከዚህ ግማሹ ያህል ሁልጊዜ እየጨመረ በሄደው በሞሮኮ— መካከል ይከፈላል:: ሆኖም አሜሪካ ለራሷ እርሻ ስለምትጠቀምበት በዓለም የዱኘ ገበያ የሦስተኛው ዓለም ድርሻ ከፍ ያለ ነው::

ይህ ዝርዝር 'ድሆች ሕዝቦች' ድህነታቸው ከመጀመርያ እርግማን ያልወጣና ሀብት በተለይ ለመሠረታዊ —ከበድ— ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ሸቀጥ እንደ ሚያገለግሉ ሊያስረዳ ይችላል:: የድህነታቸው ጦስ ወደፊት እንደምናየው ሀብታቸው ለነርሱ ኢንዱስትሪ በማገልገል ፋንታ ኢምፔሪያሊዝም ለራሱ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ስላዘረፋቸውና ስለሚዘርፋቸው ነው::

በሦስተኛው ዓለም ላይ የሚፈጸመው የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ መቀየትና እየጠነከረ መሄዱ አሉታዊ መልክ ብቻ መያዝ እንደሌለበት ማመልከት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ የኢምፔሪያሊ አገሮች የማዕድን ኢንዱስትሪዎች ከ1958 እስከ 1964 በ15 በመቶ ብቻ ያደጉ እንደነበረ ማለት ከቀረው የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚያቸው ክፍሎች በጣም ያነሱ መሆናቸውን ያሳያሉ:: ምክንያቱ: የነዚህ አገሮች የምድር ውስጥ ሀብት እያለቀ ሲሄድ ወይም ውጤቱ ሲያነስ ወይም ከዕድገታቸው ጋር ሳይመጣጠን ሲቀር የሦስተኛ ዓለም ሃብት እየበረና እየተባዘ መቀጠሉ —ቁ83 ከ1958 እስከ 1964— ነው:: ከዚህም ወዲያ የኢምፔሪያሊዝም ሰፈር እየወደቀ በሄደው በክበል ኃይል ከፍተኛ ቦታ ሲይዝ : የሦስተኛው ዓለም ቦታ በቤንዚንና በሚታሉት አዘውትሮ በመሻሻል ላይ ነው፤: እንግዲህ ኢምፔሪያሊዝም የሚቆጣጠራቸውን አገሮች የምድር ውስጥ ሃብት ለኢንዱስትሪዎች በማስፈለጋቸው ቢዘርፍ: በተራቸው እነዚህ አገሮች በእርሱ ላይ ወለዱ አገዱ አላቸው: የቧንቧውን ቁልፍ ይዘውበታል: በሚንቀሳቀሰው የዓለም ዕድገት ውስጥ ይህን ኃይል ዝቅ አድርጎ መገመት አይገባም::

<u>ለ· የፋብሪካ ኢንዱስትሪዎች</u>:— ስለነዚህም እንደማዕድን ኢንዱስትሪዎች

ስት በሀ እና በለ እንዳየነው ምንጩ የማዕድን ኢንዱስትሪዎች የማዕድን ኢንዱስትሪዎች ዕድገት ነው፡፡ የወደፊት እርምጃ መጠን ኢንዲስ በአሜሪካና በካናዳ በኤውሮፓ የኢኮኖሚክ አንድነት አገሮችና ሶሻሊስት በልሆነው መላ ኢውሮፓ —እንደፖርቱጋል እስፓኝና ግሪክ አገር ጭምር— ሲነጻጸር በበለጠ የሚያሳየው ኢንዱስትሪው ኃይል በደረጀበት ቦታ የእድገቱ መጠን ያነስ የተፈጠነ መሆኑን —ከከፍተኛ የቴክኒክና የኦቶሜሽን የተነሣ— ነው፡፡

| አገሮች | '48 | '61 | ልዩነት |
|---|---|---|---|
| ዓለም | 79 | 109 | 30 |
| በኢንዱስትሪ የተራመዱ አገሮች | 84 | 108 | 24 |
| አሜሪካና ካናዳ | 98 | 101 | 3 |
| ኤውሮፓ፡ ከሶሻሊስት አገሮች ሌላ | 70 | 112 | 42 |
| የጋራ ገበያ አገሮች | 75 | 106 | 31 |
| በኢንዱስትሪ ያላደጉ አገሮች | 71 | 111 | 40 |
| ላቲን አሜሪካ | 82 | 106 | 24 |
| ምሥ—ደቡ እስያ —ከጃፓን ሰቨ አገር ሌላ | 70 | 112 | 42 |

የሦስተኛው ዓለም በፋብሪካዊ ኢንዱስትሪ ወደኋላ መቅረት አስፈሪ መልክ የያዘ ነው፤ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት አለመቀነሱ ያሁኑ ሁኔታ የቀጠለ እንደሆነ መድኃኒት የሌለው መሆኑን በግልጽ ያስረዳል፡፡ በዚህም ላይ ደግሞ ምንም እንኳ በመላ በሦስተኛው ዓለም ውስጥ በቁጥር ለማረጋገጥ ባይቻልም ወደ ኋላ በቀሩት አገሮች ውስጥ በሚገኙት ኢንዱስትሪዎች አብዛኞቹ ያለጥርጥር ትልቁ ክፍል የውጭ አገር ሰዎች ወይም በነዚህ ቁጥጥር ስር ያሉ ናቸው[1]፡፡ ስለዚህ

1 ይህ ቃል በኢትዮጵያ በጣም ይረጋል፡በአገራችን ውስጥ የተቋቋሙት አንዳንዱ ቀላል ኢንዱስትሪዎችና አስመጪና ላኪ ነጋዶች በመላ በውጭ አገር ሰዎች እጅ ያሉ ናቸው፡፡ ጊንስበርግ ስሚት 'ማንፓወር ስትራቴጂ ፎር ዲቨሎፒንግ ካንትሪዝ፡ ሌሰን ኦቭ ኢትዮጵያ 1967፡ ብርሃኑ [illegible] የውጭ ነጋዶና የኢኮኖሚ ዕድገት በቀ ከ የቀዱ ተማሪዎች መጽሔት ቁ 1 ተመልከት፡፡—የተርጓሚው አስተያየት—



አብዛኛው ትርፍ ወደውጭ አገር በሚላክ አብዛኛውን ጊዜ ለተመዘዘኘ እድገት የማይስማማና የማይረዳ ነው፡፡ ለቀዳሚ —የካፒታል— ማጠራቀሚያም የማይረዳ ነው፡፡ ተጨማሪ የሥራ ፍሬ የተቋቋሙ ብቻ የውጭ አገር አምባዎች ብቻ ናቸው፡፡

አንዳንዱ የመጀመሪያ ደረጃ ሥራዎች የአንደ ማዕድን አፈር ይዘት ማዳበር ወይም ቀዳማይ የሚታል ማቅለጥ ያሉ ይታያሉ፡፡ በ1962 ሦስተኛው ዓለም ከ800000 ቶን የዚንክ አፈር 204000 ቶን የዚንክ ሜታል ከ700000 ቶን የአረር አፈር 370000 ቶን የአረር ሜታል አነጠረ፡፡ ሆኖም እነዚህ የሚታል ጥፍጥፎች በስፍራው ያሉትን ኢንዱስትሪዎች አይመገቡም፡ እንደጥሬ ማዕድን ሆነው ወደውጭ ይላካሉ፤ የሚጫኑት የትራንስፖርት ዋጋ በመቀነስ ኢኮኖሚያዊም ጥቅም ሲያገኙበት ስለቻለ ነው፡፡ በሦስተኛው ዓለም ውስጥ የብዙዎችን ለኢንዱስትሪ የማያገለግሉ ጥሬ ሸቀጦች ከጠቅላላው ፕሮዳክሽን ጋር በማመዛዘን ምን ያህል ለአገሩ ፋብሪካዊ ኢንዱስትሪ እንደሚጠቅሙ መወሰን መቻሉ ጠቃሚ ቢሆን አይቀርም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ከሁለት ምሳሌዎች በስተቀር ለመስጠት አንችልም፡፡

በ1961 ሦስተኛው ዓለም —የሶቪየት ሕብረት ባይጨመር— ከዓለም ጠቅላላ 165000 ቶን የቆርቆሮ ማዕድን ውስጥ 133000 ቶን ማውጣቱን ተመልክተናል፡፡ ራሱ ኢንዱስትሪዎች የተጠቀሙበቸው ግን ከዚህ አንዱ አስረኛውን ማለት 13350 ቶን ብቻ ነው፡፡ በዚያው ዓመት ያው ሦስተኛው ዓለም —የሶቪየት ሕብረትና ቻይና ባይጨመሩ— ከዓለም ጠቅላላ 25ሚሊዮን ቦክሳይት 17 ሚሊዮን አውጥቷል፤ ይኸውም 68 በመቶ ማለት ነው፡፡ በ1961 —የተጠቀሱት ሁለቱ አገሮች ባይጨመሩ— በዓለም ከወጣው ከዚህ ቦክሳይት 3720000 ቶን አሉሚኒዮም ተጠመቀ፤ ነገር ግን ከዚህ ውስጥ የሦስተኛው ዓለም ለኢንዱስትሪ ያቀለው 2.2 በመቶ ወይም 82000 ቶን ብቻ ነበር፡፡

ሐ .የእርሻ ፕሮዳክሽን፡— ጠቅላላውን የሦስተኛው ዓለምና የኢምፔሪያሊ

አገሮችን የእርሻ ፕሮዳክሽን ለማነጻጸር የሚረዱ አስረጆች ከዚህ በላይ አ ነደገለጽነው ያሉ እንደማይገኙ እናውቃለን፡፡ ሆኖም ለትልልቅ የዓለም ክፍ ሎች የእርሻ ፕሮዳክሽን ኢንዴክሶች ስለሚገኙ የዚህን ፕሮዳክሽን አስተዳደግ እርምጃ በአንዳንዱ በሌላው ክፍሎች ለማመዛዘን ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ክፍል –ኋራቀ የዓለም ክፍሎች– ምናልባት ጃፓን በሩቅ ምስራቅ ውስጥ ግብታ ይሆናል እንጂ –የሚከተለውን ሰንጠረዥ ተመልከቱ– በአ ነስ ገደል ሶስተኛው ዓለም ነው፡፡ በስድስት ዓመት በጠቅላላው የእርሻ ፕ ሮዳክሽን በሶስተኛው ዓለም ከአሜሪካና ከካናዳ ይበልጥ፡ነገ ከምዕራብ ኤው ሮፓ እኩል ወደፊት ተራምዷል፡፡ ሆኖም ቀርብቡን የአሜሪካን ልዩ የእርሻ ፕሮዳክሽን ሁኔታ ወደጎን ብንተው –ምዕራብ ኤውሮፓ ደህና መለኪያ ሲሆን ለሚችል– በጠቅላላው የእርሻ ፕሮዳክሽን አድገት በሶስተኛው ዓለምና ወደ ፊት በተራመዱት ካፒታሊስት አገሮች በአነስ ገደል ተጊዳኝ መስመሮች ይከተሳል፡፡

<u>የእርሻ ፕሮዳክሽን ኢንዴክስ በ1961–1962</u>

<u>መነሻ የ1952–53 – 1956–57 መካከለኛ– 100</u>

| አገሮች | የፕሮዳክሽን ኢንዴክስ | | ፕሮዳክሽን በነፍስ ወከፍ | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራብ ኤውሮፓ | 119 | | 111 | |
| አሜሪካና ካናዳ | 109 | | 96 | |
| ላቲን አሜሪካ | 125 | | 104 | |
| ሩቅ ምስራቅ –ከቻይና ሌላ– | 121 | 120 መካከለኛ | 105 | 102 መካከለኛ |
| መካከለኛ ምስራቅ | 122 | | 104 | |
| አፍሪቃ | 111 | | 96 | |

<u>ምንጭ</u>፡–የፋዖ ዓመታዊ እስታቲስቲክስ ሰንጠረዥ 6ለ 1963
'የዓለም የምግብና የእርሻ ሁኔታ' ሰንጠረዥ 1ለ 1964



ነገር ግን በሶስተኛው ዓለም ከፍተኛ የሕዝብ እርባታ ምክንያት የነ ፍስ ወከፉን የእርሻ ፕሮዳክሽን የወሰድን እንደሆነ ሁኔታው ያው አይደለም፡፡ የሶስተኛው ዓለም የነፍስ ወከፍ የእርሻ ፕሮዳክሽን በጣም በትንሽ ነው የ ሚያድገው፡፡ ከምዕራብ ኤውሮፓ አምስት ጊዜ ያነሰ፡ከአሜሪካና ከኤውሮፓ አ ነቧ አንዱነት ሆኖ ያነሰ ነው፡፡ እንግዲህ የረሃብ ፕሮብሌም በሶስተኛው ዓለም ውስጥ በቀላሉ ሲፈታ አይችልም፡፡ የያንዳንዱ የሶስተኛው ዓለም ሕዝ ብ የምግብ ድርሻ በፍጹም አይሻሻልም፡፡ –አንዳንዴ ጊዜ ከፍተኛ አደጋ ደ ርሶ የእህል ምጽዋት ካልተደረገ በስተቀር–

ይኸውም እስኪ የሚሆነው አብዛኛው የሶስተኛው ዓለም ሕዝብ በእርሻ ላይ የተሰማራ በመሆኑ ነው፡፡የአብዛኛው ሕዝብ ሥራ ምንም ዓይነት ተመዛዘ ኝ የወደፊት እርምጃ አይሰጥም፡ በጠቅላላው የጨመረውም በጣም በላላ ነው፡ 20 በመቶ በሰባት ወይም በስምንት ዓመት፡፡ ከዚህ የሚቀጥለው ሰንጠረዥ በሶስተኛው ዓለም በእርሻ ላይ የተሰማራውን ሕዝብ ቁጥር ትልቅነት ያመለክ ታል፡፡

| አገሮች | 1937 | 1950 |
|---|---|---|
| ዓለም –ከሶቪየት ሕና ቻይና ሌላ– | 58 በመቶ | 52 በመቶ |
| አሜሪካና ካናዳ | 23 .. | 14 .. |
| ኤውሮፓ –ከሶቪየት ሕ ሌላ– | 36 .. | 33 .. |
| ላቲን አሜሪካ | 62 .. | 59 .. |
| እስያ –ከቻይና ሌላ– | 73 .. | 64 .. |
| አፍሪቃ | 76 .. | 66 .. |

<u>ምንጭ፡</u>– የፋዖ ዓመታዊ የፕሮዳክሽን እስታቲስቲክስ ሰንጠ 4ለ 63

ነገር ግን እስከአሁን ድረስ ያተመለከትነው ጠቅላላውን የእርሻ ፕ ሮዳክሽን ብቻ ነው፡፡ በሶስተኛው ዓለም በሁለት ላይ ይከፈላል፡– ሀ ትልል

ቶች ምግብ ነክ ወይም ጥሬ ሸቀጦች አብዛኞቹ ወደተራመዱት ካፒታሊስት አገሮች
የሚላኩት፡ ለ እዚያው የሚበሉ የቀለብ የእርሻ ፕሮዳክሽን፡፡ የመጀመርያው
ፕሮዳክሽን በተለይ በሶስተኛው ዓለም ብቻ የሚበቅሉ እንዴት እንዳደገ መረዳት
ጠቃሚ ነገር ነው፡፡ አንዳንዱ አስረጃዎች እነዚሁና፡—

| ፕሮዳክቶች | የዓለም ፕሮዳክሽን በ1000 ቶን | | |
|---|---|---|---|
| | 1948 — 52 | 1961 | እድገት በመቶ |
| የካካዎ ፍሬ | 760 | 1180 | 55 |
| ቡና | 2240 | 4200 | 88 |
| ሻይ —ካሬሽና ቻይና ሌላ— | 545 | 819 | 50 |
| ዱፍን ለውዝ—ያለሬሽና ቻይና | 9600 | 13800 | 44 |
| ጥሬ ላስቲክ | 1550 —48— | 2120 | 37 |

ምንጭ፡— የተባበሩት መንግሥታት ዓመታዊ እስታቲስቲክስ 1962

በእነዚህ አምስት ፕሮዳክቶች ረገድ የዓለም ፕሮዳክሽን የሶስተኛው
ዓለም ፕሮዳክሽን ነው፡፡ብቻ በለውዝ አሜሪካኖች ትንሽ ይሰተፋሉ፡ —የዓመት
ፕሮዳክሽናቸው 800000 ቶን ነው፡፡— በአስራ ሁለት ዓመታት ውስጥ የአራቱ
መጀመርያ ፕሮዳክቶች እድገት ከለውዝ 44 በመቶ ወደ ቡና 88 በመቶ ደርሷ
ል፡፡ የዚህኛው ክፍል ዝቅተኛ ዕድገት ከጠቅላላው የሶስተኛው ዓለም የእርሻ
ፕሮዳክሽን ዕድገት ጋር ሲመዛዘን በጣም ከፍተኛ ነው፡ማለት 20 በመቶ በስም
ንት ዓመት፡፡

በላስቲክ ረገድ የዕድገቱ እርምጃ ቀጥታ አይደለም፡ ፕሮዳክሽኑ
ከ1550000 ቶን በ1948 ወደ1975000 ቶን በ1955 —+27 በመቶ—
እና በ1961 ወደ2120000 ቶን —+7 በመቶ— በማለፍ በድምር በአስራ
አራት ዓመታት ከ1948 እስከ 1961 —+37 በመቶ ከፍ ብሎአል፡፡ የዕዱ



ገቱ እርምጃ የተባዛ ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን በጠቅላላው ከቀረት አራቱ
ፕሮዳክቶችም ያነሰ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ አራት ፕሮዳክቶች ምንም አይነ
ት ውድድር ከሌላ ፕሮዳክት አልገጠማቸውም፡፡ ፍጥረታዊ ላስቲክን ግን በው
ሰራሽ ላስቲክ ይወዳደረዋል፡፡በው ሰራሽ ላስቲክ በ1961 የዓለም ፕሮዳክሽ
ን —የሶቪየት ሕብረት ሳይጨምር— ከ570000 በ1948 ወደ 2130000
ቶን አልፎአል፡፡

የሶስተኛው ዓለም የእርሻ ፕሮዳክሽን ፕሮዳክቶች በኢምፔሪያሊስት አገ
ሮች ተፈላጊነት ያላቸው ከሶስተኛው ዓለም በስተቀር ሌላ ቦታ የማይበቅሉ እ
ንደሆነ በተፈጠነ እርምጃ እንደሚያድጉ ከነዚህ አስረጆች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡
ተተኪው ኢንዱስትሪያዊ ፕሮዳክት —ላስቲክ— ሲወዳደረው የፕሮዳክቱ የዕድገት
እርምጃ ዝቅተኛ ነው፡፡ ቀናው የፕሮዳክሽን ቁጥር በእርግጥ የኢምፔሪያሊስት
ገበያ ሳቢነት ነው፡፡ የዚህ ክፍል ፕሮዳክቶች የዕድገት እርምጃ ከጠቅላላው
የሶስተኛው ዓለም የእርሻ ፕሮዳክሽን የዕድገት እርምጃ በጣም ከፍ ያለ በመ
ሆኑ የሁለተኛው ክፍል ፕሮዳክሽን —የቀለብ እህሎች— እርምጃ በጣም ዝገተኛ
ነው፡ ወይም በፍጹም አያድግም ለማለትት ያስደፍራል፡፡

ለመጠረስ ኢምፔሪያሊዝም የሚፈልጋቸውና ከሶስተኛው ዓለም በስተቀር
በሌላ ዘንድ የማያገኛቸው ፕሮዳክቶች አብዛኛውን ጊዜ ፕሮዳክሽናቸው በጥቂት
አገሮች ብቻ ተከማችቶ ይገኛል፡፡ሕንድ ቻይና ናይጄሪያና ቤንጋል ለብቻቸው
ከዓለም የለውዝ ፕሮዳክሽን 65 በመቶ ያመርታሉ፡፡ሶስት አገሮች ማለት ጋና
ናይጄሪያና ብራዚል ከዓለም ካካዎ 66 በመቶ ይሰበስባሉ፡፡ ላቲን አሜሪካ
ከዓለም ቡና ሶስት አራተኛውን ይለቅማል፡ብራዚል ለብቻው ግማሹን ያህል ይለ
ቅማል፡፡ ሁለት አገሮች ህንድና ሴይሎን ለብቻቸው ከካፒታሊስቱ ዓለም የሻይ
ፕሮዳክሽን 68በመቶ፡ የማሌዢያ ፌደሬሽን ኢንዶኔዥያና ታይላንድ ከዓለም
ፍጥረታዊ ላስቲክ 76በመቶ ያፈራሉ፡፡ከተፈለገ የዓለም ገበያዎች ይዞት በጥ
ቂቶች እጅ ሊጠበቅ ይቻላል፡፡

ከፕሮዳክሽን ጥናት በተገኘው ብርሃን ብቻ ገና ከአሁኑ ዋናዎችን አዝማሚያዎች ለመመልከት ይቻላል፡፡ የትልልቆቹ ከመሬት ውስጥ የሚገኙት ሸቀጦች ምንጭ የማዕድን ኢንዱስትሪ በሶስተኛው ዓለም ውስጥ በተፋጠነ እርምጃ እንደሚያድግና የዕድገቱ እርምጃ ፈጣን ከመሆኑ የተነሳ በሶስተኛው ዓለምና በኢምፔሪያሳዊው አገሮች መካከል በዚህ ረገድ ያለው ልዩነት እስከመቀጥ መድረሱን አይተናል፡፡ ሶስተኛው ዓለም የልማት መሣርያዎችና ለኑሮው የሚውሉ ሸቀጦች ለመፈብረክያ በጣም የሚያስፈልጉት የፋብሪካዊ ኢንዱስትሪዎች እድገት አዝጋሚ ነው፡፡ በጠቅላላው የኢምፔሪያሳዊ አገሮች የበለጠ አይፈቅንም፡ የነፍስ ወከፍ ፕሮዳክሽን የታሰበ እንደሆነ በጣም ያነሰ ነው፡፡

አስተዳደጉ በእርሻ በኩል ያው ተመሳሳይ ነው፡፡ ለኢምፔሪያሳዊ አገሮች ፋብሪካዎችና ሕዝብ የሚጠቀሙበት ፕሮዳክቶች የእድገት እርምጃ በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡ ለአገሩ ሕዝብ ቀለብ የሚውሉት ፕሮዲክቶች እያደጉም ወይም ወደታች በመውረድ ላይ ናቸው፡፡

ባጭሩ በፖሊቲካ ነጻነት አፍላ ወቅት የኢምፔሪያሊዝም ሥራና ዓላማ የሆነው የኢንተርናሺናሳዊ የሥራ ክፍያ ከመድከም ይልቅ በገሃዱ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ ለነጣቆች ጥሬ ሸቀጦች ማፍራትና ዝቅተኛ ኢኮኖሚ የኑሮ ደረጃ፡ ለሌሎች ፋብሪካዎች፡ የተፈጠነ የኢንዱስትሪ እርምጃና ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ያደላድላል፡፡



## የ መ ጽ ሐ ፍ ት ች ት

ከዉኒያለው በጋለ

### ፍቅር እስከ መቃብር

አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ 'ፍቅር እስከ መቃብር' የሚል ልብወለድ ታሪክ በ1958 ዓ.ም ማለት የዛሬ ሁለት ዓመት በብርሃንና በሰላም ማተሚያ ቤት አሳትመው አውጥተዋል፡፡ ምንም እንኳ መጽሐፉ የዛሬ ሁለት ዓመት የታተመ ቢሆንም እዚህ አውሮፓ በብዛት የደረሰ አይመስለኝም፡፡ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ በብዙዎች በተማሩና በሚማሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የታወቁ ቢሆኑ የመጽሐፉ ዜና እንኳን ቀደም ብሎ ባይደርስን እንኳ መቅረቱ እጅግ ያስገርማል፡፡ ይህን 'ልብ ወለድ' ብዙዎች ጓደኞች ያነበቡት ኖረ እንዲያውም ሠረውን የሰሙት አይመስለኝም፡፡ እነዚህን መስመሮች በመመልከት ላይ ያለ አንባቢ ሁሉ ይህን መጽሐፍ እንደምንም ፈልጎ እንዲያነበው በጥብቅ እመክረዋለሁ፡፡

'ፍቅር እስከ መቃብር' በማለት ደራሲው ለመጽሐፋቸው የሰጡት ስም ሊያሳስት ይችላል፡፡ እርግጥ፡ መጽሐፉን ከዳር እስከዳር እንደ ሐረግ የሚዘልቀውና የሚያቆናብረው የመውደድ ታሪክ አለ፡፡ ነገር ግን ይህ የፍርሰተ ምክንያት ድሩ ማያያዣው ሰንሰለት ነው እንጂ ዋናው ታሪክ አይደለም፡፡ ዋናው ታሪክ በጎጃም በባላባታዊ አስተዳደር ሥር ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩና እንዴት እንደሚያስቡ በዝርዝር የሚያሳይ የተሟላ የከበደ ጥናት ነው፡፡ እንደሚመስለኝ የመጽሐፉ ትልቅነትና ጠቃሚነት እዚህ ላይ ነው፡፡

እስካሁን ካነበብኋቸው ያማርኛ ልብወለድ መጻሕፍት ብዙዎቹ ከዲስ አበባ 'ዘመናይ' ኑሮ፡ ከቤት አዳሪ ሁኔታ፡ ከምዕራባውያን ሥልጣኔ፡ ከነዓገዱ የሕብረሰቦችን ጉድለቶች ወይም እነዚህን ከመሳሰሉ ንዑስ ጉዳዮች አልፈው የበሳገርን ኑሮ በመተንተን ሕብረሰቦችን የተመሠረተበትን ኤኮኖሚያዊ፡ ፖሊቲካዊና

በሕሳዊ አቋም አሟልተው ቢገልጡ አይቼ አላውቅም። በዚህ ምክንያት ያቶ ሐዲስን መጽሐፍ እንደመልካም አእምሮአዊ አስተያየት አድርጌ አቆጥረዋለሁ።

ማንኛውም የሥነጽሑፍ ሥራ የደረሰበትን አስተያየትና እምነት፣ ከርሱም ወዲያ የደረሰውን መደበኛ ርእዮተ ዓለም —ኢዲዎሎጂ— የግድ ማሳየቱ አይቀርም። ከዚህ የሥነጽሑፍ ሕግ የሚያመልጥ ምንም ዓይነት ድርሰት በዓለም የለም። 'ፍቅር እስከ መቃብር' የጎጃምን ሕዝብ ኑሮ፣ የባላባታዊ አገዛዝን ኢዲዎሎጂም በማሳየቱም በላይ የደረሰውን የፖሊቲካ አቋምና ሕብረሰብአዊ መደብ ሊያሳየን ይችላል። በዚች የክሪቲክ ጽሑፍ ውስጥ በረዣዥም ጥቅሶች በመጠቀም መጽሐፉ የያዛቸውን ሕብረሰብአዊ ጥያቄዎችና የደረሰውን ርእዮተዓለም እንዴት ለማየት እንደሚቻል ለመግለጽ እሞክራለሁ።

## 1 የባላባታዊ አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ አቋም

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የባላባታዊ አስተዳደርን ኢኮኖሚያዊ መሠረት ከሚገልጡት ክፍሎች ምናልባት ዋነኛው 'የባላገር መልእክተኛ' የሚለው ምዕራፍ ሳይሆን አይቀርም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በባላባቱና በገበሬው መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በግልጽ ለማየት ይቻላል። ባላባቱ ተቀምጦ በሌላው ሥራ የሚጠቀም በኢኮኖሚ ዘርፍ ምንም የሥራ ፍሬ የማይሰጥ ከላይ የሆነ መደብ ነው። ገበሬው በሁኔታው ትንሽ ከበርያ የተሻለ ቢሆንም የሚሠራው ለባላባቱ በመሆኑ ሁልጊዜ የሥራውን ፍሬ እየተቀማ ከሥር የተጨቆነ መደብ ሆኖ ይታያል። —በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው የሕብረሰብአዊ አቋም በመሠረቱ ባላባታዊ ቢሆንም የበርያ አገዛዝንም የያዘ መሆኑን እናስተውል።— ሃብታሙ ገዢው ባለሥልጣኑ ፊታውራሪ ባላባቱ ነው። ሠርቶ የሚያመጣው ግን ገበሬው ነው። ይህ ሁኔታ ከወዴት መጣ? በዚህ በተጠቀሰው ምዕራፍ ውስጥ ባላባቱ ፊታውራሪ መሸሻ ለአገልጋዮቻቸው እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ፡—



'ሸረ ለመሆኑ ....... ሸረ ለመሆኑ እነዚህ ጉልቶች የደም ዋጋ፣ የነፍስ ዋጋ መሆናቸውን አታውቁምን? ከያቶቼ አበስኔ ተራራ ዘረን ወንዝ ተሻገረን፣ አቀበት ወጥተን፣ ቁልቁለት ወርደን፣ በሩቅ በቅርብ ዘምተን በጦር ሜዳ ደረታችንን ለመድፍ፣ አንገታችንን ለሰይፍ ሰጥተን፣ እንዲህ አድርገን ያገኘናቸው የነፍሳችን ዋጋ እንጂ እዚ ቁጭ ብለን ሆዳችን እስኪነፋና ብስና እስኪይዘን እየበላን እየጠጣን ፍየልና ጥሻ ዝንጀሮና ጦጣ ወይም አህያ እየጠበቅን ያገኘናቸው አለመሆኑን አታውቁም?' —ገጽ 211—

ጉልቱ የተገኘው ፊታውራሪ ወይም አባት አያቶቻቸው ተከትለውት በተዋጉለት ንጉሥ ነው። በመሬቱ ላይ የሚኖሩት ገበሬዎች በቆሳንደል በገልጋይነት ከነመሬቱ ለፊታውራሪ የተሰጡ ቢሆኑ ያለሕዝቡ ፍላጎት ሕዝቡ ባይጠየቅ እንዲሁ ተሹመው ከላይ ተጭነውበታል። ስለተዋጉ ወይም አያታቸው ስለተዋጋ ፊታውራሪ በባላባትነታቸው ከመሬቱ የሚመጣውን ፍሬ ቁጭ ብለው መብላት እንጂ እንደ ባላገሩ ሞፈር ቀንበር ተሸክመው ላባቸውን አንጠፍጥፈው መሥራት አይኖርባቸውም። 'ፍየልና ጥሻ፣ ዝንጀሮና ጦጣ ወይም አህያ' መጠበቅ —ማለት ሥራን መሥራትና ፍሬ ማስገኘት— ለባላባቱ መደብ ትልቅ ጸያፍ ነው። የባላባቱ መደብ በመዥገርነቱ ከገበሬው የሚቀማውን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከባላገር መልእክተኞች አንዱ በዝርዝር እንዲህ ሲል ይገልጻል፡—

> 'ዘመን ከተለወጠ በስስቱ ጉልቶችዎ የምንኖር ድሆችም ለመስቀል ስስት ለገና ስስት ፍሪዳ ከብቶቻችን ሸጠን ከፍለናል። ይህም ርስት የሚያርስ አርቦ፣ በጉልት ተቀምጦ የሚያርስ በሬ ከምንከፍለው ሌላ ነው። በዚህ ላይ ለወረዳ፣ ለምስለኔ፣ ለጭቃ ሹም የምንከፍለው የገንዘብና የጉልበት ዕዳ አለ።
>
> ገጽ 212

የባላባታዊ አገዛዝ ኢኮኖሚያዊ መሠረት መሬትና ገበሬው ናቸው። ጭቃ ሹሙ መልከኛው ምስለኔው የወረዳና ያውራጃው ገዥ እስከንጉሡ ድረስ የሚኖረው ገበሬው ሠርቶ በሚያፈራው ቢሆን የሹመቱ መብላል ከላይ እስከታች በዘመቻ

የዚህ ዓይነቱ ሕብረሰብ ሕይወትን የሚያራዝመው የባላባቱ ጉልበትና ጭቆናም ቢሆንም ገዢዎቹ አቋቸውን የሚያጠነክሩበት የኢዲዮሎጂ ድጋፍና ምስክር ያስፈልጋቸዋል:: ይህንንም የሚያገኙት አንደኛ ዘር በመቁጠር ሁለተኛ ቤተ ክህነትን የጭቆና አገዛዝ ኢዴዎሎጂ አቀራቢ በማድረግ ነው::የዘር ቆጠራና የቤተ ክህነት ኢዲዎሎጂ አቀራቢነት የአቶ ሐዲስ መጽሐፍ ከሽፋን እስከሽፋኑ ሞልተውት ይገኛሉ:: እነዚህ ጣምራ የጠቋሚ ኢዲዎሎጂ ምሰሶችን በብዙ ጥቅስ ለማስረዳት ይቻላል::

በገጽ 83 'ፊታውራሪ በባላባትነታቸው እጅግ የሚኩሩ መኮንን ነበሩ:: ከትግሬ ከሸዋ ከጎንደር ነገሥታት ጋር ያላቸውን ዝምድና ቁጭ ብለው እንደው ዓቢ ማርያም መድኃም የጀመሩ እንደሆነ ስሚ የሚሰለቸው አይመስላቸውም' የሚል ጽሑፍ ይገኛል::በዚህ ጽሑፍ ላይ ፊታውራሪ ስለሰውልጅነታቸው ሲናገሩ 'ገዛታችን ከኛ ተወስዶ ለገበሬ ለነጋዴ በጥጥና በቆዳ ሊሸጥ ይችላል፡ ለበቶቻችን ከነገሥታቱ የወረስነው አቀንትና ደም ግን መሠረቱን የማይለቅ ከነፍስና ከሥጋችን ጋር ጠብቆ የተሠራ በገዛታችን ጋር ለገበሬና ለነጋዴ ሊሰጥ የማይችል ነው::'ይላሉ::

በባላባታዊ አገዛዝ ሥር የዘርና የዝምድና ነገር ለኢዲዎሎጂ ምሰሶዎች አንዱ በመሆኑ ንጉሥም ያባት ያያቶችን ተረት እንደምንም ገፋፍቶ ለሰቡና ከበሰፊው ማድረስ የግድ ይሆንበታል:: በሁኑ ሕገመንግሥት ውስጥ ይህ ተረት የያዘውን ከፍተኛ ቦታ እናስታውስ::

ቤተ ክህነት የነገሥታቱና የባላባት መደቡ የጥቅም ተካፋይ እንደመሆኑ በሃይማኖት አመካኝቶ ይህን ርዕዮተዓለም ተጨቋኙ ሕዝብ እንዲቀበለው ትሰብካለች:: ለዚህ ማስረጃ ከቶ ሐዲስ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ለመጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ምናልባት ያበ ምገቢ ነገር ሁሉን የሚያጠቃልል ባይሆን አይቀርም:-

'ጌቶች ያሉት ሁሉ እንዴ እንዲ ስህተት የሰውም ሁሉም እውነት ነው::እግዚአብሔር ጌታን [illegible]



ጌታው ገዥው ፍርድ ቢያጓድል ድጋ ቢበድል ጠያቂው መንግሥት ከዚያም በላይ እግዚአብሔር ነው እንጂ ድጋ አቤት ከማለት አልፎ የሚተዳደርበትን ሕግ እግንና ፈሪጅ ሆኖ አያውቅም::አሁን በሳገር አጼም የሚሠራው ከቀጋብ በቀር ሌላ ስም የላሉ አበምቤ:: —283—

ይህ አይዲዎሎጂ ሕዝቡን አፍዝዞ አደንዝዞ የሚደርስበትን ጭቆናና ግፍ ውርደቱን የበታችነቱን ወሰን በሌለው ትዕግሥት እንዲቀበለው ለማድረግ የተፈጠረ ርእዮተዓለም ነው::በዘብህ ስለንጉሥ ነብር ቢያስላስል ከዚህ ቀቀሱ ያለውን ትርጉም ይሰጠዋል::

'ሕዝብ ከሰውነት ወደ እንስሳነት ደረጃ ራሱን ዝቅ አድርጎ ተገፍቶ ተጣቅቶ የሰውነት መብቱንና ክብሩን ሁሉ ትቶ የማይበላ ነገር በልቶ ተገፆ ተደቅድቆ ለንጉሥ የሚገዛ መሆኑን የሚያሳይበትና ንጉሥም ያገ እያዩ ደስ የሚሰኙበት ዘዴ ነው::' —454—

ነገር ግን ጭቆናው ከመጠን አልፎ ተጨቋኙን ያንገፈገፈው እንደሆነ ገበሬው እንዲሸፍት ግድ ይሆንበታል::በመጽሐፉ ውስጥ የተነገረው የአበጀ በለውና የባላገሩ መሸፈትም ለዚህ አንዱ ምሳሌ ነው::ወጣም ወረደም የሚሸፍተው ሕዝብ በገዢው ኢዲዎሎጂ ቦታ የሚተካ የራሱ ኢዲዎሎጂ ስለሌለውና አነደገዢው መደብ ትክክለኛ የፖሊቲካ አመራር ስለማያገኝ የጭቆና አገዛዙን ከነድሬቱ ሊያጠፋ አይችልም::

በቤተ ክህነት አማካይነት ለተጨቋኙ ሕዝብ የሚሰጠው ርእዮተዓለም ሕዝቡ ራሱ ያለውን ታላቅ ጉልበት እንዳይገነዘበው አእምሮውን ሸፍኖ አያዩ እንዳያይ የሚያደርገው ማደንዘዣ ነው:: የባላባቱ መደብ በዚህ ስብከት የሚጠቀመው ሕዝቡ አንድነት በተነሳ ጊዜ እንደማይቻለው አቀብሎ ስለሚያውቅ ነው:: ቀኛዝማች አከሉ ስለባላገር መሸፈት ሲናገሩ 'ያዳው ባላገር አሸንፋለሁ ብሎ ማሰብ ውቅያኖስን ጠልቼ አጠርባለሁ እንደማለት ነው' ይላሉ:: —227— የአቶ ሐዲስ መጽሐፍ 'ልምድ ወግ ስራት'በማለት የሚ

ያቀርባቸው ሁሉ የባላባታዊ ገዥዎች ርእዮተዓለም መሆናቸውን አንባቢው እንዲገነዘበው፡፡

### 3 ጉዱ ካሳና የደራሲው ርእዮተዓለም

'ፍቅር እስከ መቃብር' በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የደራሲውን ርእዮተዓለም በመወከል የሚናገር ብዙውን ጊዜ ጉዱ ካሳ ነው፡፡ ደራሲው አንዳንዱ ህም በበዛብህ አማካይነት አስተያየታቸውን ቢሰጡም —ሰምባሌ አሳይ ሰለንጆ ገብር በተጠቀሰው ቦታ— ዋናው ወኪላቸው የተማረው የተመረመረው ጉዱ ካሳ ነው፡፡ ጉዱ ካሳ ምን ዓይነት ሰው ነው?

ጉዱ ካሳ በትውልዱ የባላባታዊ መደብ አባል ነው፤ ነገር ግን ከመሬመዩ የተነሳ የሕብረሰቡን ባላባታዊ አቋምና አሠራር ሊረዳው ችሏል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የሕብረሰቡን ዋና ዋና ጠባዮችና መልኮች የሚያስረዳን እርሱ ነው፡፡ ምንም እንኳ አስተባሰቡ የሚወሰነው በ'ልምዱ' ላይ ቢሆንም የሕብረሰቡን ኢኮኖሚያዊ አቋም በመጠኑ የተረዳ ምሁር ነው፡፡ ጉዱ ካሳ ከመጠን በላይ የሚያጠቃው ገላሰበኝነቱ ነው፡፡ ከሕብረሰብ ኑሮ ተለይተው በተዋራ ዓለም ውስጥ በመኖር የወረሩ የከንቱ ፍልስፍና እንጂ የተግባርን የሥራ ነገርን እንደማያውቁት ሁሉ በእውቀቱ ያለበትን ሕብረሰብ ለመለወጥ እንዲትሟት እንኳ አያነሳም፡፡ የርሱ ሥራ ስብከት ነው፡፡ ሕብረሰብን በስብከት ብቻ ያሳገዳት ተጋድሎ ለመለወጥ የሚቻል ይመስለዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በዙርያው ያለችውን ዓለም ብቻ እንጂ የታሪክን ግሥጋሴ ሕግ ሊገነዘበው አይችልም፡፡ የጉዱ ካሳን ገላሰበኝነት በደንብ ከሚገልጹት ጥቅሶች የሚቀጥለውን እንመልከት፡—

> ስለዚህ ካሳ ዓሥጨ የማህበሩን አርጌ ስራት ጠልቶና ነቀፍ ባርጌ ስራት ብርያ የሆኑትን የማህበሩ አባሎች ነቶና ተጠይፍ ሸፍቶ —— በበበበው ዓለም ውስጥ የገሉን ዓለም ፈጥሮ በበው መካከል ብቻውን የሚኖር ሰው ነው፡፡ —123—



ከዚህ ከጦርሂ የገለበብ ፍልስፍና የተነሳ ጉዱ ካሳ ጨቋኝነም ተጨቋኝም በገዱ ዓይን ይመለከታቸዋል፡፡ ትግልና ተጋድሎ ሥራው በላይደለ የታሪክን እንቅስቃሴ በሚገባ ስላልተረዳው የገዘ ራሱ አስረኛ ስለሆነ ገና በይዋጋ የተሸነፈ ፍጡር ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ ለበዛብህ የሚናገራቸውን ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ቃላት እንመልከት፡—

> '—— ከንቱ አሰበ ከንቱ [redacted] የሚናገር ዘመናይ ከሉ እየተደነቀ ገዥ እንዲሆን ቀም ነገር አሰበ ቀምነገር የሚሠራ የተናቀ ሆኖ ተገዥ እንዲሆን ተመድቧል፡፡ይገርማል፡፡ ይህን የሚይረብ ልምዱ ይህን በገፍ ላይ የተመሠረተ ክፉ ልምዱ ተመልከትህ እንዲህ ያለ ስራት ሲኖር የሚገባውም የሚችልም አይደለምና ይልቅ አወዳደቁ እንዓይከፋ ቀስ ብሎ እንዲለወጥ ማድረግ ይሻላል ብለህ የተናገርህ እንደሆን እንደከሐዲ ተዋቀረህ የምትበቀልበት ገመዱ ይበናዓልሃል፡፡ —— ደግሞስ ይህን ሁሉ የሚያደርጉ ክህ የጌታ ዘር ነን የሚሉት ሁሉንም ረገጠው አላይ የተቀመጡት ብቻ ቢሆኑ ቀቀማቸው አንዓይጊደ ልባቸው ነው ትላለህ፡፡ነገር ግን ባሮች፡ አጋስሪዎች፡ሎሌዎች ሁሉ ገፍ የሚሠራባቸው ሁሉ ከገፍ ሰሪዎች ጋር አንድ ላይ ተባብረው ሲፈር ቅብህ ምን ትላለህ?' —334—

እዚህ ላይ የጉዱ ካሳ አስተሳሰብን በቀርቡ መመልከት ያሻል፡፡ከገልስበኝነቱ የተነሣ ባላባታዊው የሕዝብ አቋም ከነድራጁ እንዲወረም አይፈልገም፡፡ቢፈራ ቢችሮ ብቻ አንዳንዱ የስሳሜ ለውጥ አሰቦችን አያቀረበ ለዚያው የመደቡ ሰዎች ባይሰጡት ያልፋሉ፡፡ እንደውነቱ ከሆነ ግን ይህን 'እንደ በግ መንጋ በፊቱ የሚሄደውን ተከትሎ የሚጎጋ' —123— እያለ የሚስዱበውን ተጨቋኝ ሕዝብ አይፍርበውም፡ በርግጥ ለርሱ ደህንነት ለመሥራትም ለመሠዋትም ምንም ምኞት የለውም፡፡ የያዘው የፍልስፍና አስተያየትና የትውልዱ መደብ እንደመጨና ጠፍረው ይዘውታል፡፡

ይህ ባይሆን ኖሮ እንዳበጀ በለው የተጠቂውን ወገን ወስዶ የራሱን ጥቅም ባይፈልገን የሚዋቹንና ዘራፊዎችን በተቋቋመ ነበር፡፡ከደመ ነጻ ነኝ በማለት እንዲመቸው ጨቋኙንም ተጨቋኙንም ጠላቶች አገሩን አየወሰዳቸው

በተለይም ተጨቋኞችን በሐሰት ይዘባቸዋል። እርግጥ እርሱ እንደሚለው ተበደኝ ሕዝብ ሰውቶ የማይፈልግ ቢሆን ኖሮ እንደአበጀ በለው ─እንደበላይ ዘለቀ─ ያሉ ጀግኖች በየጊዜው ሕዝቡን እያስከተሉ ሰመነሳት ባልቻሉ ነበር። ታዲያ ነጋሰበኛው ጉዱ ካሳ ይህን ሁሉ እውነት አጭበርብሮ ሰማለፍና ያነበቢውን ልብ ወደራሱ ለመሳብ 'አይ፣ እርሱ ብቻውን ምን ያድርግ?' እንዲባል ለማድረግ ይሞክራል።

## መደምደሚያ

አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ 'ፍቅር እስከ መቃብር' የሚተርከው ታሪክ 'አበይ ለየሳው የመኪና መንገዱ፣ ሰወንዙ ድልድይ ሳይሠራለት' የነበረውን የጎጃም ሕዝብ አኗኗርና አስተሳሰብ የሚያሳይ ነው የሚሉ ይመስላሉ። ዘረስ ምን ተለውጧል ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ የጎጃም ሕዝብም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ያህል እንዳልተራመደ መገንዘብ አያዳግትም። የአቶ ሐዲስ መጽሐፍ የዘረውን የበስት ፋቡን የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ እንደሚገልጽ ከበላ በታቹው መደብና ካህናት መኳንንት በስተቀር ሊከደው የሚደፍር ያለ አይመስለኝም። ብቻ ይህ እንኳን ከአርእስታችን ውጭ የሆነ በሌላ ቦታና በሌላ ጊዜ ልንነጋገርበት የምንችል ጉዳይ ነው። አቶ ሐዲስ በመቅድማቸው ውስጥ መጽሐፋቸው:─

'ብዙ ጥሩ ደርሰቶች ያልያዙት መልክቶች ሳንባቢዎች ለማድረስ የተበናዓች ስለሆነችና በተለይ የኢትዮጵያን አንባቢዎች ለሚያበስቡ አስከዛሬ ደረስ መልስ ሳላገኙ እንዳገዱ ጥያቄዎች መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አሳቦች ይዞ ስለምትቀርብ አንባቢዎች ሳይስለቹ በማስተዋል እንዲመለከቷልኝ ተስፋ አደርጋለሁ' ይላሉ።

ይህን ካሉ በኋላ ከጥያቄዎች አንዱ የፊደሉች ሁኔታ መሆኑንና ለዚህም መልስ ለማቅረብ የሞከሩ መሆናቸውን ይገልጹልናል። ነገር ግን ማንኛውም ይህን መጽሐፍ ያነበበ ሰው ቀንኞች የኢትዮጵያ ጥያቄዎች የፈደልን



ጉዳይ የማይመለከቱ መሆናቸውን እንዲሁም ደራሲው ያቀረቡት ታሪክ ─በራሳቸው አነጋገር─ 'ዘመን ዘመን የሚያከክል' ሌላ መዓት ጥያቄ እንደሚነባ ይገነዘብ አይቀርም። ለነዚህ ከላይ ለተዘረዘሩት ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ሕብረሰባዊ ችግሮች አቶ ሐዲስ ምንም መልስ አልሰጡም፤ ሊሰጡም አይችሉም። በደፈናው በጉዱ ካሳ አፍ አድርገው ሥርዐተ ማህበራችን ተሸሽሉ መሠረት አለበት እያሉ የሚሰነዝሩት አስተያየት ምንም መፍትሔነት የለውም።

በዚህ ባንፃሩ እንደታያቸው አድርገው የባላባታዊ አስተዳደርን መልክ እንደ ስዕል ስለው በተጣራና በሚያስደስት አቀራረብ መግለጻቸው ብቻ ትልቅ አስተዋፅኦ መሆኑን አንመነሳቸው። ተበሩፍቶ በተለመደው የኢትዮጵያ ደራሲያን አድርበይ ፍልስፍና ባይመሩ ቀርተው መጽሐፋቸውን ለንጉሡ ነገሥቱ አለማበርከታቸው 'ጃንሆይ ኖሮ እንዲህ ነበር፣ ዛሬ ግን በርስዎ አርቆ አስተዋይነትና ታላቅ መሪነት ይኸው አገራችን ዘመናዊ ሥልጣኔን ተቀዳጀች' አለማለታቸው፣ የንጉሡን ፎቶግራፍ ከመጽሐፉ የውስጥ ሽፋን ላይ አለማስቀመጣቸው፣ በዚህ ሁኔታ መጽሐፉ ራሱ ሊታተም መቻሉ፣ ይህ ሁሉ የደራሲውን ግምት ከፍ የሚያደርገው መሆኑን አንርሳ።

የአቶ ሐዲስ መጽሐፍ የባላባታዊ አስተዳደርን መልክ እንደ መስተዋት ወለል አድርጎ የሚያሳይ ስለሆነ ነገሩ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲያነበው ያስፈልጋል። አንባቢው ከዚህ በላይ በጭሩ ከተጠቀሱት ሐሳቦች የበለጠ ትምህርትም ሊያገኝበት ይችላል።

## ከ ደ ብ ዳ ቤ ሣ ጥ ና ች ን

በዚህና ወደፊት በሚወጡት የታጠቅ ቅጦች ያንባቢዎቻችንን ደብዳቤዎች ለማተም ወስነናል፡፡የሚደርሱን ደብዳቤዎች ሁሉ በጣም አጭር እንዲሆኑ እደራ፡፡በሚታተሙት ደብዳቤዎች ላይ የጻፉት ሰዎች ስም አይገለጽም፡ ነገር ግን አንዳንዱ ሰዎች ስማቸው እንዲገለጽላቸው በተለይ ከጠየቁ ይህንኑ ለመፈጸም ዝግጁ ነን፡፡

---

ለታጠቅ አዘጋጅ፡

'ከሕዝብ ወደ ሕዝብ' የሚለው እውነተኛ የሆነ የፖሊቲካ መስመር ስላሆነ የተሰማኝ ቀረታ ፈጽሞ የለም፡፡ ...... ይህ መሠረታዊ ሐሳብ ምን ጊዜም የማይዘበ ለመሆኑ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ጭንያለው በጋለ ያቀረበው የመጀመርያ ውይይትና አንተም ያበራረኸው መሠረታዊ ሐሳብ የያዘ ከመሆኑም በላይ አዲስ ከፍተኛ የፖሊቲካችን መስመር ለማመልከት የላቀ የአይዲዮሎጂና የአስትራቴጂ መንገዱ የከፈተ መሰሉ ይታየኛል፡፡

ከአሜሪካ

የዘንድሮው ታጠቅ በጣም ጥሩ ነው፡፡ግን ምን ይሆናል የደረሰን ኮፒ ቁጥር በጣም አነስ፡፡ታጠቅ ጥሩ ነው ስል ርዕሰ አንቀጹና ስለነሣዎች የተጻፈው አምዱ ጥሩ ነው ማለቴ ነው፡፡ሌላውን ግን በፊትም ያየነው ነው፡፡

ከአሜሪካ

ታጠቅ ጥሩ ነው፡፡ርዕሰአንቀጹ፡ የሞንታርጋም ውስኖች፡ ስለነሣዎችና እንዲሁም ገጣሞች አልፈህ አልፈህ ጣል ጣል ያደረግሃቸው ምስሎችና ቀኖች ጽሑፎች ለመጽሔቱ ደህና ገጽታ ይሰጡታል፡፡ .....ርዕሰ አንቀጹ በጣም ጥሩ ነው በተለይም ከአምናው ጋር ቢመዛዘን፡፡ሆኖም አንዳንዱ



ጥያቄን ግድፈቶች ይታዩበታል፡ ለወደፊቱ ግን መጠንቀቅ ነው፡፡በአስተባበሩም ላይ ዲያሌክቲኩን የበለጠ መሣርያ ለማድረግ መሞከር ያስፈልጋል፡፡

ከአውሮፓ

በርዕሰ አንቀጹ በመሠረቱ እስማማለሁ፡፡ነገር ግን በርዕሰ አንቀጹ መጀመርያ ገጽ ላይ በለአቤቶታ የጠቀሰኸው ጉዳይ ከዓላማችን ጋር የሚዛነፍ ይመስለኛል፡፡በገጽ አራት ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት መታወጁን አበሰርተናል ብለሀል፡፡እንደምታውቀው አዲሲቱን ኢትዮጵያን የሚያስፈልጋት ሕዝባዊ መንግሥት መሆኑን ከተገነዘብን በኋላ የዚሁም በሠራተኛና በገበሬ ላይ የተመሠረተው ሕዝባዊ መንግሥት አቋምና ተግባር ምን መሆኑንና ሊከተለው የሚገባውን መስመር አሳየን እንጂ ሕዝባዊ መንግሥት አቋቁመናል የሚል አዋጅ አላወጀንም፡፡ለዚህ ገና አልደረስንም፡፡ሕዝባዊ መንግሥቱን የሚያውጀው ሕዝቡ ራሱ ነው፡፡

ከአውሮፓ

---

### ልዩ ልዩ ጉዳዮች

በበርሊን የሚታተመው የማህበራችን የወር መጽሔት 'ትግላችን' በየወሩ ባይታጎል ሊወጣ በመቻሉ በጣም ተደስተናል፡፡በተለይም በኢትዮጵያ የሚፈጸሙትን የነጻነት ትግሎች ተከታትሉ ዜናውን በሃተታ ሊያበግን ስለቻለ 'ታጠቅ' በተለይ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡በመጽሔቱ ላይ ሠፍረው የሚገኙትን አምዶች በተለይም የሊቀመንበር ማኦንና የቼን ጥቅሶች የሚያነቡ የሚያበሳስሉ ሁሉ ስለነጻነት ትግል ትክክለኛውን መሣርያ በአርነቱ ሊያ

ገኙ ስለሚችሉ አንባቢዎች ሁሉ 'ትግላችንን' ከራስጌአቸው እንዳያርቁት እንመክራቸዋለን::

---

በዩጎዝላቪያ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻችን ተማሪዎች የውስጥ ማህበር በቅርቡ ሊያቋቁሙ መቻላቸውን በመግለጽ በቀጥታ ከፕራግ ጽፈውልናል:: የማህበሩ መቋቋም ወሬ በጣም ያስደሰተን መሆኑን እየገለጽን ሥራቸው በሚያስደስት አኳኋን እንዲሰምርላቸው 'ታጠቅ' ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል::

---



NATIONAL UNION OF ETHIOPIAN UNIVERSITY STUDENTS
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

April 5,1968

To Ethiopian Students in Yugoslavia,
To all other Ethiopian students in Europe, North America and elsewhere.

Dear Brothers,

We the Ethiopian students here at home are bringing to your attention the crisis facing the Ethiopian student movement here. The University administration which is dominated by the Anglo-American clique - headed by the CIA agent J.C.N. Paul, academic vice president of the Universit has closed the University and has put all campuses in Addis Ababa under the control of the police force. Students are forcefully evicted from their hostels and many are brutally beaten and arbitrarily jailed. Many high schools and elementary schools including members of the public sympathized with us were brutally beaten, harassed and jailed. Strangel enough, the police force has closed public places where students could be accommodated after the closure of the University campuses. Among the many students illegally imprisoned are: The Secretary General of the NUEUS of Addis Ababa, the president of the USUAA, the Editor-in-Chief of the Union's paper STRUGGLE and nine other student leaders. Reports from some students who visited the prisons indicate that the student leaders are being tortured inhumanly.

Our two prominent student organizations - NUEUS and USUAA and the reputed paper STUGGLE are declared banned for having refused to work for American interests. Students who voiced their independent views on international issues contrary to American imperialist interests are threatened with expulsion from the University.

Student patriots who oppose Ethiopian interests are being being cynically undermined by American advisors are being be rsecuted by the Ethiopian security force who are, no doubt misguided by American groups in the University.

Patriots who are working for the well-being and development of our country are being hunted by the police

because the Americans are misleading the Government that our student movent is controlled by communist organization. To prove this unfouded and irrational speculation the security and the University authorities broke into our Union offices and ransacked our files. American specialists have also taken photographs of our files along with the Ethiopian Security Police.

The pretext used by the imperialist clique to undertake the purging of our patriots was that some students (about 400) have resisted cultural aggression by a fashion show of Western dresses put up in the University on the 30th of March. But this incident was not violent enough to warrant the closing of the University and the persecution of patriots. The Ethiopian students here are determined to carry the struggle through to the end until final victory.

Please communicate this message to the Ethiopian Student organizations in Europe and North America as soon as possible. And please send a photocopy of this letter to the IUS secretariate for disseminatinn to its members.

Long live the beloved country!
Long live our student movement!

With fraternal greetings,

(Signed)

ABBAY ABRAHA

Acting President of NUEUS

N.B. Five civilians and one high school student are so far officially reported killed by the police during the fight in Addis this week.



## WE STAND UNITED

The stand of the administration under the leadership of J.N.C.Paul, an American, has been made clear through the University Reporter of Monday April 1, 1968. Paul is of the opinion that the University is "being run by a small number of well-organized students." He added that the University will never be opened "with USUAA in existence," and the University cannot be run "under this state of tension." The University Reporter also revealed that the students who participated " in this thing will never be allowed to return to the University." It added that the students under police custody "will be brought to account."

This, then, is the position taken by the University Administration. Their pretext for taking such far-reaching reactionary measures was the Fashion Show incident. In their attempt to mislead the public, Ato Wubshet Dilnessahu and Paul deliberately lied and distorted events. This is, after all, part of their character. Nevertheless, the measures undertaken were planned beforehand and are part of an intrigue to prevent students from exercising their democratic right in electing their student Unions and thereby destroy the will of the students and isolate them from the backward community of which they are part and parcel. We have recognized the attempts of the University Administration to strangle the student Union,ever since it was established, through various intimidations and threats.

Paul has made it clear that the University will "never be opened with the USUAA in existence." USUAA is a Union that has been voted into office with the approval of the majority of the University students of Addis Ababa. It has been chartered by the University and it is a legal body. As a matter of fact, it was Paul who first inaugurated USUAA. In short,USUAA is a chartered Union representing the University students of Addis Ababa.

Regarding the Fashion Show incident, USUAA officers made it clear to the Administration officials verbally that the USUAA had no hand in it, that it was not sanctioned by the Union and that the Congress of the Union had never met to discuss the issue and thus was a venture

of individual students to oppose peacefully what they thought was wrong. In fact, some of the "honourable guests, the ambassadors' wives" hurled insults at the students like "dirty, filthy niggers" and "you Africans are hopeless," and the like. This understandably led to subsequent clashes. The allusion that every protest is organized by a small group of well-organized students is an insult to the entire student body and our nation in general because it has beeb forgotten that every student has the capacity to think independently regardless of the intention of a "small group." In fact it is the Administration that is being run by a "small well-organized group" with Paul as its head, and not the student body.

The Police, with habitual savagery, arrested students who were not in any way connected with the incident from street corners, offices, hostels and even from shower rooms and other places both within and without the campus. The case of Hailu Mengesha, President of USUAA and Tsegaye G. Medhin, Editor in Chief of STRUGGLE and many others are vivid examples that the incident was a pretext to execute a premeditated plan to immobilize the students. The University students of Addis Ababa will never let down their brethren in prison. The officers of USUAA and the Editor-in-Chief of STRUGGLE were put in office by the University students of Addis Ababa and it is to these same students that they are responsible and not to the master officers of the Kolfe Camp. We will have our students in prison released whatever the cost.

The conditions stated in the University Reporter by Paul are totally unacceptable to the University students of Addis Ababa. We would like to remind Paul and others that the students are the most important segment of the University and that it cannot exist without them. Without students there can be no University.

We, the University students of Addis Ababa, have elected a Union, viz. USUAA, to represent us. We have elected officers of whom some are behind prison bars. We have overcome many hurdles in the past and no obstacle is strong enough to stand the might of a united student body. The supreme test has come and we are ready to face it as resolutely as ever. This latest attempt is designed to ban student Unions forever and leave us at the mercy of the authorities. The challenge has been flung at us. We are ready to meet it, united and with one voice.